

2ኛ ዕትም

# ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር ::

ኤፍሬም ሥዩም

# ፍቅር
# እዚህ ቦታ
# ፈገግ
# ብሎ ነበር

@Smatch81

በ ኤፍሬም ስዩም

2005 ዓ.ም.


ሙሉ የባለቤትነት መብቱ የተጠበቀ ሆኖ በጽሑፍ በተሰጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ፣ ይህን መጽሐፍ እንደገና ማሳተም ፣ መቅዳት ወይም መተርጎም አይቻልም።

ያለ የጽሁፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐብሐር ሕግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 የስነ ጽሁፍና ኪነጥበብ ሥራዎች ባለቤትነትን በተመለከተ ከአንቀጽ 1647 እስከ አንቀጽ 1674 በተደነገገው መሰረት ካለሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ አንድ አንቀጽ እንኳን መልሶ ማሳተም ፣ መቅዳት ፣ ወይም በሌላ መልክ ማሳተምና ማሰራጨት አይፈቀድም።

ከዚህ ሕትመት ጋር በተያያዘ በባለቤቱና በሕግ ያልተፈቀደ ተግባር የሚፈጽም ማንኛውም ሰው ለሚያደርሰው ጥፋትና ጉዳት በወንጀልና በፍትሐብሐር ሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ስራዎች በአጠቃላይ የኤፍሬም ስዩም ናቸው።

የሽፋን ሥዕል እና ዲዛይን በ አማኑኤል ተገኔ



© አንቶኒዮ ፊዮረንቲ

ተበረከተ

ለ ሶልያና

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| አመሰግናለሁ ፩ | ሀ |
| አመሰግናለሁ ፪ | ሐ |
| ጠማረ አሚን | ሠ |
| ዋዜማው | ኀ |
| ቅድመ ታሪክ | አ |
| ስለተ ቅዳሜ ፒያሳና ቦሌ | 1 |
| ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር | 6 |
| ፍርሃት | 10 |
| በቀደም ሜክሲኮ | 11 |
| ከዘጠኝ ወር ኋላ | 12 |
| እልህ | 13 |
| 'ምንድን' | 14 |
| ________ | 15 |
| እንባር | 16 |
| ነበር | 17 |
| እንባር ፪ | 18 |
| እንባር ፫ | 19 |
| ዛሬ | 20 |
| አላዋቂ ሳሚ | 21 |
| ፍርሃት ፪ | 22 |
| አቦል | 23 |
| ፪ ጊዜ ፫ | 24 |

| | |
|---|---|
| የአልቦ አሻራዎች | 25 |
| ከብዙ ገጽ አንዱ | 26 |
| ሕልም | 27 |
| በረከ | 28 |
| 10:30 | 29 |
| የክረምት ሽሽት | 30 |
| ገጽ 31 | 31 |
| አሑን | 32 |
| እውነት ወደ ኋላ | 33 |
| ነበርን ወደፊት | 34 |
| ነበር ወደ ኋላ | 35 |
| ከትላንት ወዲያ | 36 |
| መስታወት | 37 |
| መዝሙር ለአያቶች | 38 |
| ገጽ 39 | 39 |
| ላርባ አንድ ፊሪ | 40 |
| ገጽ ከዚህ በፊት | 41 |
| የበር ጩኸቶች | 42 |
| መስታወት ፪ | 43 |
| በመታየት ማየት | 44 |
| ከእኔ ለእኔ | 45 |
| ፩ ጊዜ ፫ | 46 |
| ግለ ታሪክ | 47 |
| መጠሪያ ለ______ | 48 |

ድንጋይ በድንጋይ ላይ 49
ቀጥሎ ላንቺ 50
ላንቺ 51
ማንምና ምንም 53
ግማሽ-ባዶ ሙሉ 54
ቀዝቃዛ አቦል ቤት 55
ገጽ አርባ በገሃድ 58
የሰባ ዓመት ንጉስ 59
ላርባ አንድ ፈሪ ጀ 60
እንድም ሦሥትም 61
በድጋሚ ለ_____ 62
ላይንና ለጆርሽ ሁለት ሥጦታዎች 63
ምንምን ዳግመኛ 65
ገጽ 39 እንዳዲስ ዳግመኛ 67
ናፍቆት 68
ገጾች 69
ይህ ርዕስ አይደለም 70
የማ'ሊን ፈገግታ ገጣሚ ሲያለቅሰው 71
መግቢያ 74
ጊዜ 75
ብዙ ገፆች 76
እሱ ባንቺ ቦታ 77
ምልከት 78
ሕልምሽ ትዝ ሲለኝ 79

ሌላ _____ 80

አዛኝ ቅቤ አንጓች 81

አንፃር ፱ 82

ዕለት 83

ጥቂት ስለራሴ 84

ክብር ወይስ 85

ሰተተኛ እውነት 86

ደባል ታቦት 87

መቼም 88

ተራ አስተያየቶች 89

የራስ ምስል በራስ 90

ስንብት 91

ሁሉም ከንቱ ነበር 92

ምንም 93

የ ________ ቤት ግጥም 94

ዳግም ስለ ትችት 95

ሐያሲ 97

መውጫ ወዳሻችሁ 101

እመሰግናለሁ . . .

ሲልዚ ፋንታ (MA VIE) ፣ ፋሲል ረታ ፣ ዳንኤል ታዬ(ሠንሊ) ፣ ዳዊት እድነው(ሠንሊ) ፣ ሠለሞን ባህለ (ገጣሚ) ፣ ዩሐንስ ሃ/ሚካኤል (ገጣሚ) ፣ ሕዝቅኤል ሰብሰቤ ፣ ኤርምያስ ኋሁልሰገድ ፣ ሰለሞን ሀጋ-ዘአብ ፣ አማኑኤል ተገኔ ፣ ሳሙኤል ታዬ ፣ ምልዕቲ ኪሮስ ፣ አምስት ኪሎዎች (ማርያም ፊትለፊት) . . .

ቤተሰቦቼ -

እናቴ ማሜ አገደው ፣ ሙላቷ አድነው ፣ ታደለ ተረፈ ፣ በልዩ ኃይለሥላሴ ፣ ዘመድኩን ፍቃዱ ፣ ላቀች ዜጋ እንዲሁም ለዓለም ሰዩም የእናንተን ለእናንተ መናገር ራሴን በራሴ ከማክበር እኩል ስለሚሆን በልብ ከልብ ለልብ

4ኪሎ ሮሚና ባርና ሬስቶራንት ተቀምጬ ነበር። በረንዳው ላይ ሕዳር 11-2004 . . . (የሚካኤል ዋዜማ) . . .

አንድ ሰው ወደ'ኔ ጠረጴዛ ተጠግቶ 'ይቅርታ መቀመጥ ይቻላል?' አለኝ . . . ፈቃዴ ነበር . . .

ተቀመጠ።

ስለ-ተለያዩ ጉዳዮች . . . ሥለ'ኔ ቀዳሚ ስራ እወጋን . . . ሥለሚቀጥሉት ጠየቀኝ . . .

በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ . . . ያ-ሰው . . . (ይህ ወጣት) አሁን እጃችሁ ላይ ያለውን መጽሐፍ. . . አሰናዳው. . . አሳመረው . . . በዚህ ሰው አልባ ወቅት ውስጥ እንዲህ አይነት ሰው ማግኘት መታደል ሲሆን በተራ የቃላት ስልፍ ውስጥም ቀናነቱን ለማስቀመጥ መሞከር ብልግና ባይሆንም ድፍረት ግን ሊሆን ይችላል . . . በአጭሩ እነሆ ሰውዬው

## ዘሚካኤል

በሚካኤል . . . ዋዜማ . . . እውነትም ዘሚካኤል . . . 'ዘ' ለኔ የተሰጠ ቅዕል ይመስለኛል ታላቅ አክብሮትና ምስጋና . . . ለወዳጄ ይሁን።

ጠማሪ አሚን

ሁላችንም የግላችን የሆነ sound track አለን። ያ sound track ያለፈ ጊዜያችን የአሁን ማንነታችን ነው። ኢሁንን የሚረብሽ sound track አለ። ድሮ ተቀነባብሮ እስካሁን ድረስ የሚደመጥ። በግድ። ከቀጭን የሸንበቆ አንደበት የሚፈስ ማሕዘኒ ቅላጼ ያለው የጊዜን ሕግ ሽሮ ከትላንት እስካሁን ያለን ማንነት አለን... በዚሁ ድብልቅነት ደግሞ አሁን የራስዋን ዜማ ከቀጫጭን የከራር ገመዶች በምንነት እየመዘዘች ነው... ዕዝኖቻችን ግን ሁለቱንም በዕኩል የድምጽ ከፍታ ማዳመጥ አይችሉም እንደኛው ከፍ ይላልና...

ከአሁን ቅድም... ከዛሬ ትላንት... ከአምና ካቻምና የተሻለ ቢሆንም... መልካምና ውብ የነበሩት ያለፉት ጊዜዎቻችን ግን ከአሁን የበለጡ ሊሆኑ አይችሉም (አሁን መልካም ባይሆንም እንኳ)።

የቅድሙን ውብ ሙዚቃ የተጫወተው ድምጻዊ... አሁንም እየተጫወተ ነው... ሥንተኛ track ላይ እንዳለ ባለውቅም... ሸክላው ግን እየተሽከረከረ ነው... በመጀመሪያውና በሰባተኛው ሙዚቃ መካከል ግን የዜማ የሙዚቃና የሐሳብ ልዩነት በፍጹማዊነት አለ... ሕይወት ከሚሽከረከረው የሙዚቃ ሸክላ ልዩ አይደለችም... ሸክላው ሐዘንተኛ ሐሳብ ያላቸውን ሙዚቃዎች ተሸክሟል... ማሕዘኒ ዜማ ግን በዉበት ሲሰራ ዉብ ነው።

መቼም ሕይወት ላይ የሚያናድድ ነገር አይጠፋም አይደል?... ትናንሽ የሸክላ ጭረቶች የሙዚቃውን ጣዕም ይረብሹታል... ከሙዚቃው ሐዘንተኛ መንፈስ ይልቅ ባላዋቂ ጥፍር የተቧጨሩ የሸክላው ጀርባዎች... ዜማውን ያበላሹታል... አንድ ወዳጄ... ዉብ እኔነቱን ብዙ ምርጥ ዜማዎቹን በማንነቱ ላይ እንደተሸከመ ራሱን በራሱ ለመስበር ሲሞክር ሞክሮም ተሰባብሮ ... ሥብርባሪው ተለቅሞና ታሽጎ ወደ ዘልዓለም ፀጥታው ሲጓዝ ተመልከቻለሁ... በዚህም ከታላላቆች መስበር የታናናሾች ጭረት እንዲጎዳ አስተውያለሁ...

እንግዲህ አሁንን ለመኖር ያለፈን ተራኪ የሆነው የ sound track ድምጽ መቀነስ አለበት። ትረካውንና ማጀቢያ ሙዚቃውን ዕኩል ለማዳመጥ የተፈጥሮ ሕግ አይደለምና። መድረክ ላይ የቆሙት ሁለት ተዋናዮች በተመሳሳይ ደቂቃ ዕኩል ቢናገሩ አንድም ቃለ ምልልሱ የንዴት ጩኸት መሆን አለበት አልያም ስህተት ነው።

መደንበርና መበርገግ የሚመስል በግራና በቀኝ የሚደበደብ ጎርናና

እና ስስ የድራም ድምጽ ያጀበው ማንነት አለ... የተቀጠቀጠ ጀርባው እስኪጠና ድረስ የትላንቱን የድራም ዱላ እና... ድብደባውን በማሰብ 'እንደምን ያለ ተራ ሙዚቃ ነበር?' ብሎ ተራውን ሙዚቃ እስከዛሬ ድረስ የሚያደምጥ... መሽከርከር የማይችል ቢሽከረከርም ማንነቱ ላይ አንድ አይነት ዜማ አንድ አይነት ቅንብር አንድ አይነት ሐሳብ የሆነ... ሥልቹ ዘፈን ዘፈኑ... ዘፈኑ ትላንት ነው። ሙውዬው ግን አሁን። ይህ የዚህ ሰው sound track ነው። በሕይወት ብርቱ ከንድ የተመታ ማንነት።

አሁንና ቅድም ፣ ዛሬና ትላንት ፣... ዕለትና አምና... እኩል አይደሉም። የአሁን ማንነታችን ግን በአምና ሙዚቃ የታጀበ ነው። ዕዝኖቻችን ባረጀና በነተበ ፍቅር በተረሳም የትዝታ ዜማ የታጨቁ ናቸው... (የተረሳ ትዝታ)... ስላለፈ ማንነት አሁንን ማጣፈጫ ቅመም እንጂ ያለፈን ማስታወስ አይደለም... ብዙዎቻችን ግን ባለፈ ትውስት ፈንጠዝያ ውስጥ ስለምንዋልል ከአሁን ፈገግታችን ይልቅ የአምና ኩርፊያችን... ከዛሬ ሳቃችን በላይም የጠቻምና ዕንባችን የቅዕበት አኗኗታችን ጋርደውታል መጋረጃው ግን መገለጥ ያለበት ከውስጡ ያለውን ለመመልከት ዓልያም የእኔነትን መቅደስ ለማፅዳት መሆን አለበት...

በገዛ አመለካከታችን (አስተውሎት) ራሳችን በራሳችን ላይ ያደረስነው በጣቶቻችን የሕይወታችን አጃቢ ሙዚቃ አለን። በሰዎች ለስላሳ ጣቶች እንዴት እንደተነኩ ሳናውቅ ተነክተው ተዳስሰው ና ተጭነው የሚውሁ ፒያኖ የሚመስሉ... ማንነቶችም አሉን (እኒህ ድምፆች ትላንት የተደረሱ የዛሬ ማንነቶቻችን ናቸው) ቢሆንም ሕይወት ሕልሞቻችንን ወደ ቅዠት ብትለውጥብንም እኛ ትላንት የተገኘን ነን እንጂ ዛሬ የተወለድን አይደለንም ከተወለዱ በኋላ ሕይወትን ከልደት ቀን ጀምሮ መቁጠር ዕድሜን ከሕልውና የመቀየጥ ሥህተት ነውና። ስለዚህ የዛሬውን ለአሁን ተወው 'ንጂ ትላንትን ከዛሬ ጋር አትደባልቀው።

አዳዲስ ሙዚቃዎችን እያደመጥኩ ነው... ሽከላው እኒህን ሁሉ ሙዚቃዎች መሸከሙ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚያሰማኝ አናዳጅ ሙዚቃዎች ዉበት ግን እያስገረመኝ ነው። እጅግ በጣም የማረኩኝን ሙዚቃዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርጌ እያዳመጥኳቸው ነው...

አልፎ አልፎ ከጎዳና ወደ ጆሮዬ የሚደርሱ መንገደኛ ድምጾችን እሰማለሁ... አሁን ላይ ያለ የእኔነቴ ሃሳብ በሚሰሙት ድምጾች አልተረበሸም... ድምጾቹን ቢሰማም ለማዳመጥ የስገዙ መሳከው ከፍት አልነበሩምና ይህ ማለት ግን ድምጾችን ከመኖርና ከመሰማት እያግዳቸውም እኚህ ድምጾች በሕይወታችን ላይ አልፎ አልፎ እንደሚከሰቱ ጭረቶች ሊሆኑ ይችላሉ... አልፎ አልፎ ጭረት ቢኖርም የሽከላውን ሙዚቃ ሊያውከው

ይችላል። ቁስለቱ የዳነ ጠባሳም ከሚመረቅዘው ልዩ ነው...

እኔ ብዙ አይነት sound track ያለኝ የአሁን ሰው ነኝ። የትናንቱንም ቅጽበት ሕይወት እንድትሞላ የማደርገው ትላንትና አሰሮ ሊገዝኝ የሚሻውን አጃቢ ሙዚቃ የጨኸቱን መጠን በመቀነስ ነው። በሕይወት ሰሌዳ ላይ ጽፈነው ያመጣነው ሙዚቃ የድምጽ ሃይል ሊቀንስ እንጂ... መጥፋት አይችልምና።

ትዝታ (ወደ ኋላ መፍሰስ) ትላንትን ዛሬ ላይ ከመመኘት የሚመጣ ነገር ነው። ዛሬ ላይ አብረውን ያሉትን ሰዎች ወደ ኋላ አናስባቸውም... ትላንት የተዉንን (የተውናቸውን) ሰዎች ግን ዛሬ ላይ ልናስባቸውና ልንመኛቸው... ወደ ኋላ እንፈሳለን ከወንዙ ወደ ምንጩ... ከደረስንበት ወደ ተነሳንበት... በዛሬ ሰወነት በአሁን እግር ላይ ቆመን... የድምጹን መጠን ቀንሼ የማደምጠው አንድ ብቸኛ የኔ ብቻ የሆነ Jazz አለ... ርዕሱም 'አንቺ ብቻ' የሚል ሲሆን እርሷም እርሷ ናት። ይህን ሙዚቃ እኔና እርሷ ካቻምና አቀናብረነው እስካሁን ድረስ የማዳምጥበት ምክንያት... ከዚህ ከፍ ያለ አቅም ያለው ሙዚቃ እስካሁን ለጆሮዬ ባዳ ስለሆነ ይሆናል... ቢሆንም ያሙዚቃ ያምራል ማለት ይህኛውን ማጣጣል አይደለም የተሻለ ነው ማለት 'ንጂ...

የዚህ ቅጽበት መዝሙሬ እርሷ ብትሆንም እኔ የአሁን ሰው ስለሆንኩ የትላንትና ልበልበና... የረጋ ፈሳሽ ወንዝ ነበረውን ውቡን የዉበት Jazz አንቺ ብቻ ለእኔ የሚለውን የድምጽ መጠን እጅግ በጣም ቀንሼዋለሁ። የአሁን ሰው ስለሆንኩ።

ይሕን ሙዚቃ በሰማሁት ቁጥር ጊዜ በሕሊና ላይ ሃይል እንደሌለው እረዳለሁ ጊዜ ማለትም ትላንት... አምና... አልያም _ ካቻምና ምስላቸው ሁኔታቸው በአይምሮ ላይ ብቃት የላቸውም እላለሁ... (ድፍን አምስት አመት ሆነኝ። እርሷን ከተመለከትኳት። ሙዚቃውንም ለሦሦት ዓመት ያህል ሰርተን ከጨረስነው) እንግዲህ ይህን ሙዚቃ... እስካሁን ድረስ መስማት እሻ ነበር... ያለምንም መደባለቅና መደባለቅ።

ይህን የሁለታችንን የJazz ሙዚቃ ሰርተን እንደጨረስን ዋሽንት የነበረውን ሸምበቆ እንጨት ነው ብዬ ሰባበርኩት... በባከሰፎኑ አንደበት... አየራ በተንኩበት... በአናቱም የትዝብት ጢስ ወጣ... እርሷ ግን 'ይህ ዉብ የJazz ሙዚቃ ከነዚህ የተገኘ ነው' አለችኝ እኔ ግን የአሁን ሰው ስለሆንኩ 'በአዲስ መሳሪያ አዲስ ሙዚቃ እፈልጋለሁ' ብዬ የተኛኝበት የተቃኘውን ተጫውቼ ግንባሯ ላይ! ለመጨረሻ ጊዜ... ግንባሯን ተሳልሜ ወጣሁ... እንግዲህ ከአምስት ዓመት በኋላ እርሷን

ሳስብ ትዝ የሚለኝ ሙሉ ጨረቃ የሚመስል ገላዋና ግንባሯን ስስም የነበረው አይኗ አስተያየት ብቻ ነው። ከአምስት ዓመት በኋላ እንደ ከአምስት ዓመት በፊቱ ትታየኛለች። የጊዜ ሕግ በህሊና ላይ ሃይል የለውም። ይህ ሁሉ ቢሆንም ከዛችኛዋ ትዝታ ይልቅ የዚህች ዝግ ያለ የጠዋት ዝናብ የመሰለ ጭቅጭቅ ያዘለ ሙዚቃ የተሻለ የድምጽ ከፍታ አለው... የዛችን ብሰማም የዚህችን አዳምጠዋለሁና።

እንግዲህ እርሷ (ያቺ) ማለት በእኔነት መደብ ስቆም ትላንት?... ከትላንት ወድያ አምና ካቻምና... ካምስት ዓመት በፊት ብቻ ናት። አሁንና ይህ ቅጽበት ግን እኔ ነኝ። እኔ ፍጻሜው ምን አይነት እንደሆነ ባለውቅም የነገን ሙዚቃ ዛሬ እያቀናበርኩኝ ነው። ልዩነቱ ቀዳሚዋ ሸክላ ከጨረቃና ርጋታ ካለው ሃይቅ ስትሰራ... ሁለተኛዋ ግን ከጉም ከጢስና ከገርፍ የተቃኘች ናት።

ሸክላው እየተሽከረከረ ነው... ስለጨረቃና ስለረጉ ሐይቆች ያቀነቅን የነበረው ሙዚቀኛ አሁን ደግሞ ከጉምና ከጢስ ከገርፍና ከድፍርስ ዉሃ ስለምትመሳሰል እንስት እየጮኸ ነው። በልቤም ከቅድሙ የአሁኑ ዜማ ከብደት እንዳለው ይሰማኛል።

... ከአስቀያሚ የጥበብ ቀሚስ ስር ውብ ና ጠንካራ ቀጫጭን የሐር ክሮች አሉና። መፈሰስ ብቻ በሆነ የሕይወት ሕግ ውስጥ... ፀሐይና ጨረቃን መገደብ መሞከር (መመኘት) እርሱ ተራ ስንፍና ነው። ተራ ሰነፎችም የድሮ ዜማቸውን እስከ አሁን ያደምጡታል... ለራሳቸው ተራ ሽንፈትም 'ትዝታ' የሚል ተራ ስያሜን ይሰጣሉ... በሰነፎች የሕይወት መመሪያ ውስጥ 'ወንዙ ሳይደርስ መንገድ ላይ መቆም ይችላል' መንገድ ላይ መቆም ይቻላል የሚል መመሪያ ያለ ይመስላል።

እኛ በጊዜ ውስጥ አይደለንም... እኛ በራሳችን ጊዜዎች ነን። በማንነታችን ወቅት ውስጥ ክረምትና በጋ... ጸደይና መኸር አሉ... ይህ በተፈጥሮ ሕግ ብቻ ሳይሆን በህልውና ምንነታችን ውስጥም አለ... ነፋሳት እያለን... የክረምት ያህል ጭጋጋማና ጭቃማ የሆነ ሕይወትን ልናልፍ እንችላለን። በእሳትነታችን... በተፈጥሮ ሕግ ከተመሰልንበት የጸደይ ብርሃናማና አበባማነት ይልቅ... እንደ መሬት ልንሆን እንችላለን። በጉብዝናችን የሸበትን ፣ በምርኩዛችን የጎለመስን ልንሆን እንችላለን። የሕይወት የወቅቱ ሁደት ከየትኛው እንደሚጀምር... ወዴት እንደሚፈስ አናውቅም... በሕይወትና በተፈጥሮ ፍርርቅ መካከል ልዩነት ስላለ...

በሕይወት ሕግ የኖርናቸው ዕለታት ገድለናቸው የመጣናቸው ፊሳ ወቅቶች ናቸው ወደ ፊት የሚመጡት ደግሞ ለመሞት የተዘጋጁ ጊዜያት...

1... 2... 3... መስከረም... ሐምሌ... ነሐሴ በየትኛው የዜማ ዓይነት ታጅበናል።

ሙዚቃው አራራይ ወይም ፍሱሐዊ ዜማ ሊኖረው ይችላል። ዝማሬው ግዕዝ ወይም ዕዝል ይሆናል... እኔም እኚህ ጣምራ መሃል አራት አይኖቼ ስምንት ጆሮዎቼ ሊመለከቱና ሊያስተውሉ ሊያደምጡና ልብ ሊሉ የሚሹት 'አሁን' የሚል ሙዚቃዬን ነው...

'አሁን' የሚለው ሙዚቃ ምንም ዕንኳ ከድፍርስ ውሃ... ከጢስና ከጉም... እንዲሁም ነጠብጣቡ ከበዛ ጨቅጫቃ የዝናብ ድምጽ ቢሰራም... ከተፈጥሮ ሳይሆን ከሕይወት ሕግ የተቀመረ ስለሆነ... እርሱን ማጣጣም እፈልጋለሁ...

'አንቺ ብቻ' የሚለውን ሙዚቃ... ልቀንሰው ነው። በአማናዊና በምሳሌያዊ መሃል ልዩነት አለና... ሕይወት ላይ የተቀነባበረ ሙዚቃ... መጠኑ ይቀነሳል እንጂ ፈጽሞ መጥፋት አይችልምና ያንን ቀንሼ ይሆን እያሰላሁት ነው!። ካቻምና ብሰቅም... የካቻምና ሳቁ የአሁን ፈገግታዬን እንዲጋርደው አልሻም። እኔ የአሁን ሰው ነኝና። ሙዚቃ ደግሞ ስሜትን አይከተልም... ሙዚቃ ስሜትን የሚያዝ ሌላ ስሜት ነውና... አረጋውያን ለወጣቶች በሆነ የሙዚቃ ሃሳብ ይውረገረጋሉ... ወጣቶችም ኖረው ባላጠነጠኑት የሙዚቃ ሃሳብ ኮረዶቻቸውን አቅፈው ግንባራቸውን ይቋጥራሉ... እኔም እንዲሁ ነኝ...

ከድፍርስ ውሃ የተጠመቀው የሕይወት ሙዚቃ ነፍሴን አላቆሸሻትም። ከትነትና ከጉም የተጨመቀው መንቻካ ዝናባማ ሙዚቃም አልቀዘቀዘኝም... ሙዚቃ የግል ሥሜትን ሳትከተል ስሜትን እንደምታዝ ሁሉ... የሕይወት ወቅታዊ ዑደትም እንዲያ ነውና... ሸክላው እየተሽከረከረ ነው...

ቅድም ሲያቀነቅን የነበረው ሙዚቀኛ አሁንም እየተጫወተ ነው። የ'አሁን' ሙዚቃ አቀናባሪም የቅድሙን ሲጫወት የነበረው ነው... ሸክላው መሽከርከሩን አላቆመም...

እየተሽከረከረ የነበረው ሸክላ እየተሽከረከረ ቢሆንም ሲጫወት የነበረውን 'አሁን' የሚለውን ሙዚቃ ግን ፈጽሟል። አሁን ምንም አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ የለም። የዘፈን ቃልና ዜማም እንዲሁ። ሸክላው ግን እየተሽከረከረ ነው። ያለ ድምጽ... (ሽሽሽ... ድምጽ ብቻ)

ጸጥታው አሁን ያለው የጊዜ አካል ነው። ይህች ድርጊት አልባ ጊዜ የሕይወታችን 'ትድምርት' ናት። በምንም ውስጥ የሚሆን ሁኔታ። ሁኔታው ግን ምንም ነው። ያለ ሙዚቃ ድምጽ እንደሚሽከረከረው ሸክላ...

ቀ

ያለሁኔታዎች የሆኑ ሁኔታዎች አሉን። እዚህ ጸጥታ መሐል 'ሕይወት ያለተግባርና ያለድርጊት ሕይወት ናት' የሚል አሳቤ ወደ አስምሮዬ መጣ። (ከነበረው ሃሳቤ የተጋጨሁ ይመስለኛል)።

የሆነ ነገርን አለማድረግ ወይም ምንም አለማሰብ አለመኖር አይደለም። የጊዜ ብክነትም አይደለም። ምንም አለማድረግ ከንቱነት ከሆነ ያ ከንቱነት በራሱ የህልውና አካል ነው። ሽከላው ያለ ሙዚቃ ድምጽ እንደሚሽከረከር ሁሉ... ያለ ተግባርም ሆኑ የሕይወት ጊዜዎች አሉን።

በሽከላው ውስጥ ያለው የጸጥታ ጊዜ በራሱ የሽከላው የሕልውና ክፍል ነው። ያለተግባር የሆኑ ጊዜዎቻችንም በሕይወታችን ውስጥ ያሉ የሕይወታችን... ሕይወቶች ናቸው።

ፀጥታ ቀጣዩን ድምጽ መጥሪያ ደወል ነው። ትንንሽ ዝግታዎች ረዥሙን መንገድ የመጀመር... ሃይል የማከማቻ መንደርደያዎች ናቸው። ስለዚህም ምንም አለማድረግ የሆነ ነገር የማድረግ ሂደት ነው። ምንም የተደረገ ባይኖርም ዕንኳ... ሊደረግ የሚታሰብ አለ።

ቀጣዩ ሙዚቃ ምን እንደሆነ ባላውቅም... ባልሰማውም... ሽከላው ግን ከጸጥታው ኋላ የሚያሰማኝ ነገር እንዳለ አውቃለሁ። ቀጣዩ ሙዚቃ ግን አሁን ከማስተውለው ባዶነትና ዝምታ ግን አይበልጥም። አሁን ያለችው አሁን በምትመጣው አሁን እስትከደን ድረስ።

በሽከላው ተምሳሌትነት የማያት የሕይወቴ ባዶ የሆነች ባዶ የጊዜ ክፍል በራሷ ድምጽ ናት። በራሷ ሁኔታ ናት። በራሷ ድርጊት ናት... ምክንያቱም በፊደሎች መሃል ያሉት ክፍተቶች የፊደላቱ ውበቶች ናቸውና። ለምሳሌ አንድ የተወደደ ከቡር መፅሐፍ እያነበብክ ነው ብለን እናስብ... መፅሐፉ እንዲህ ይጀምራል...

'የሆነ የሚወደድ ክቡር መፅሃፍ እያነበብክ ነው። እያነበብክ... እያስተዋልክ... እየተገረምክ የሆነ ምዕራፍ ላይ ልትደርስ አንድ ገጽ ይቀርሃል።... የጀመርከውን መፅሃፍ አጋምሰህ የደረስክበትን ጨርሰህ... የጨረስከውን ሥትገልጥ አምስት መስመር ፅሁፍ በስተግራህ በኩል ታገኛለህ።... በስተቀኝ በኩል ደግሞ ምዕራፍ ሰባት ብሎ የሚጀምር ይታያል። ለመጨረስ... ሰባተኛውን ለመጀመር... አምስቱን መስመር ጀመርክ...'

'የዕረፍት ስሜት ሳያስፈልገው አይቀርም። በድንግዝግዝ የማየት... ምንምን የማስተዋል ሁኔታ ውስጥ ነው። በእጁ ከያዘው መፅሃፍ ተነጥለው ሩቅ የተጓዙ ዓይኖች... ያለ ፊደል

የሚያስብ ማንነት . . . ምን እንደሚያስብ የማያውቀው ‘እኔነት’ ውስጥ ነው። በምንሙ ውስጥ ነቃ ወይንም ከምንምነት ነቃ . . . ወደ ተገለጠለት አስተዋለ . . . አንድ ሊያደርገው የሚገባ ነገር አለ . . . የተቀባው . . . የተሰጠው . . . እነርሱም እነዚህ ገጥሞች ነበሩ . . . ’

ኤፍሬም ሰዩም

ከደመና ልትቀዳ ተራራውን ወጣች

የመዝገቡ ተሰማን አድባር የሚለውን ሥዕል አስታወስኩት። ሕልሜን ሳስታውሰው በሕልሜ እንደዛ ያለ ተራራ ጫፍ ላይ ነበርሽ። ልብስሽም ስዕሉ ላይ ያለውን ነጭ የመሰለ ጥበብ ነበር። ከጥበብ ቀሚስሽ መሃል ከጭንሽ አካባቢ እጆችሽን እየላክሽ ብዙ ቀጥር ያላቸው ከመዳፍሽ መጠን ችሎታ የበዙ እፋዬ ገላዎች ወደ ቀልቀል ትለቂያለሽ ከተራራው እግር ሥር ረዥምና ሰፊ ሐይቅ ወይም ባህር አለ እፋዬ ገላዎቹ ፍፃሜያቸው ወደ ጥልቀ ነበር። እጅሽን ወደ መቀነትሽ አካባቢ ትልኪያለሽ የማያልቁ እፋዬ ገላዎች ትዘግኛለሽ ሕልሜ በሕልሜ ይገፋም ነበር። በሕልሜ ከተገረምኩበት ሕልም መካከል ልነቃ ስል ልባንን ስል በስተመጨረሻ ያስተዋልኩት እፋዬ ገላዎቹ መቀነትሽ ነበሩ ወይም መቀነትሽ ከእፋዬ ገላ የተሰራ ነበር። ረዥም የእፋዬ ገላ መቀነት ወደ ባህር እየተዘገነ የሚወድቅ።

"ልሄድ ነው" ትይኛለሽ በሕልሜ

"ወደ የት?" እኔ እጠይቅሻለሁ

"ወደ ተራራው እናት" ብለሽ አሁንም እንደ ቅድሙ እየዘገንሽ እና እየጣልሽ መጓዝ ጀመርሽ

እኔ የት ሆኜ እንደማወራሽ ሥፍራው ትዝ አይለኝም ፤ የሚታየኝ የአንቺ ብቻ ነበር። ውሃ ባወዛው ጠይም ድንጋይ ላይ በባዶ እግርሽ ወደ እናቱ እየተጓዝሽ ሳለ ድምፄን አሰምቼ ጠየቅሁሽ . . .

ወደ ተራራው እናት ለምንድ ነው የምትወጪው? አልኩሽ ከዚህ ጥያቄ በኋላ ብዙ አዳዲስ የአለት ስንጥቆች ተመልከቻለሁ አንቺም ወደ ፊት እየተራመድሽ ወደ ኋላ መለሰ ብለሽ . . .

"ተራራውን የምወጣው ከዳመና ለመቅዳት ፈልጌ ነው።" ብለሽ የማያልቀውን ጀመርሽ የበተንሻቸው እፋዬ ገላወዎች ወደ ባህሩ አንቺ ወደ ተራራው እናት። ከደመና ልትቀጂ። ያሳዝናል እኔ እዛው እንደቆምኩ ነቃሁ በገዛ ላቤ ተጠምቄ ወደ እናቱም ወደ እግሩም ሳልሆን እዛው እንዳለሁ ነቃሁ ግን እንደ ነገርኩሽ እዛ መሆኔን እንጂ የቱ ጋር እንዳለሁ በፍጹም አላውቅም። ይህን ሕልም ልነግርሽ ገና ማለዳ የበተስኪያን ደውል ሲሰማ ከምንጣፌ ተነስቼ ኪዳን ልታደርሺ ወደ በተስኪያን ልትሄጅ ስትይ ላገኝሽ ሕልሜን ልነግሽ ሕልሜን ላስተረጉምሽ ከደጅሽ ቆሜ ነበር።

የቤትሽ በር ሲከፈት ያስተዋልኩት የዮፍታሔን ሰለት የመሠለ ነገር ነበር። አንቺ ጥቁር አጭር በጣም አጭር ውስጥ ልብስ ለብሰሽ ነበር ከጎንሽ ከንቱነት ከንፈርሽን ተሳልሞ ሲሠናበትሽ ያኔ ዐይኖቹ አስተዋሉሽ ዐይኖችሽ ልብ አሉኝ። ሕልሜን ማስተርጎምና መናገር አስፈላጊ አልነበርም ሁሉም ሆኖና ተተርጉሞ ነበር . . .

ከደመና ለመቅዳት ተራራውን መንዝ ከጭን ሥር የሚበተን እፋዬ ገላዎች . . .

በቆምኩበት የተመለስኩት ወደ ሕልሜ ጎልጎታ ነበር። ግን እኔ የት ነበርኩ? በዚህ ስፍራ የቱጋ?

እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ረሃሙን የሕልሜን ትርጉም እየተረተርኩ የተተረተረውንም እየጠቀለልኩ . . .

እነሆ . . .

## ቅድመ ታሪክ

ማግባት ምፈልገው
አሪፍ ገንዘብ ያለው
ምርጥ ቪላ ያለው
ሐብታም ነጋዴ ነው ማለትሽ መልካም ነው።
በተዘዋዋሪ
እንደዚህ ዓይነት ሐሳብ
ሊፈጠር 'ሚችለው ከቆንጆ ሴት ላይ ነው . . .
ይህ ማለት ምንድ ነው? . . .
እንዲህ ዓይነት ሐሳብ በብዛት ሚሰማው
በየቡና ቤት ነው።
ስለዚህ . . .
በዛም አለ በዚህ
አንቺም በውበትሽ የምትፈልጊው
የቡና ቤቷም ሴት የምትፈልገው
ቪላና ገንዘብ ነው።
ታዲያ በዚህ አገር - የፍቅር ማደሪያው የትኛው ልብ ነው?

29-02-2004

ስለተ ቅዳሜ ፒያሳና ቦሌ

ቀጭን ወገቧ ላይ
ከአንገብርቷ በላይ ልብሷ ተንጠልጥሏል
የወርቅ መስቀሏ
ጡቶቿ መካከል ዘንበል ብሎ ወድቋል
መንገድ ላይ ያየኋት
የማላውቃት ሴት ናት።
ወደት እንደምትሄድ ባሳቤ ገመትኩኝ
አንድ የቀጠራትን ወንደላጤ አሰብኩኝ
ሠባት እንቁላሎች
ግማሽ ኪሎ ሥጋ . . . (ገዝቶ)
ከርሷ ጋር ካልሆነ
ቡና አልጠጣም ብሎ አሥሬ እያዛጋ
መጽሐፉን ከፍቶ
በሩን ከፍት ትቶ
መልሶ መላልሶ ሠዓቱን እያየ
የሚጠብቃት ሠው
ሐሳቤ ውል አለው
ምክንያቱም ቀኑ ቅዳሜ ነው።
-
እርሷ አለፍ እንዳለች
መሐሙድ ፊት ለፊት
አራዳ ሬስቶራንት
አራት ጎረምሶች ሰባት ምግብ አዘው
ለመመገብ ሳይሆን
ምግቡን ለመጨረስ እጅትን ተጣድፈው
በቆየ ጋዜጣ
የተጠቀለለ ምናምን አስቀምጠው
ፊት ለፊቴ አሉ
ምግቡን ሳያኝኩት ቶሎ መጉረሳቸው
አራት ሆነው ሳሉ ዝም ማለታቸው
ገባኝ ሁኔታቸው
ምክንያቱ ምንድን ነው?
ቀኑ ቅዳሜ ነው።
-

እግሬን ለማፍታታት እየተራመድኩኝ
ወደ ሆነ መንደር በድንገት ገባሁኝ
የሆነ በራፍ ላይ
ውስጥ ልብስ ያረገች
ልብስ አጠባ ውላ ትንሽ የደከመች
ፀጉሯን ልትሰራ
ጓደኛዋ ጭን ስር ሽጉጥ ልጥፍ ያለች
እግሯ ከፈት ያለ
ጡቷ ወረር ያለ
የአንድ እጇን መዳፍ
በስተግራ በኩል የፀጉሯ ክፋል ላይ
የአንድ እጇን መዳፍ
ከፍት እግሮቿ መሃል
አንገቷ ወደላይ
ረፍት የሚመስል ሰማዩ ላይ ወድቋል
አይኗ ከሩቅ አልፏል
እፎይ . . . የሚል ፊደል ገላዋን በሞላ
እንደ ልጅ አቅፎታል
የዚህ ሁሉ ነገር
የዚህ ሁሉ ዉበት ምክንያቱ ምንድን ነው
ቀኑ ቅዳሜ ነው።

-

እዚህ መንደር ጫፍ ላይ
አንድ ያቧራ ሜዳ ከሩቅ ይታየኛል
እንደ መዝሙር ሆኖ
የሕፃናት ጩኸት ወደኔ ይመጣል
ከሜዳው መሃል ላይ አቧራው ይበናል
ሕፃናት ነበሩ አበቦች ነበሩ
ምሳቸውን ትተው
በጨዋታ ምሳ ጠግበው የሰከሩ
ምክንያቱ ምንድን ነው
ቀኑ ቅዳሜ ነው።

-

Oslo በረንዳው ላይ
አንድ ጥቁር ቡና ከተቆራጭ ጋራ
በቀኙ ጋዜጣ

ገራ እጁ ጣት መሃል ሮዝማን ሲጋራ
ቀልቡን ጋዜጣው ላይ
የሲጋራውን ጢስ ከጋዜጣው በላይ
ቡናውን ሲጎነጭ ንባቡን ሲያቆም ዐይኖቹ ውብ ሴት ላይ
እያቀያየረ
በልቡ ባሳቡ እያመነዘረ
Oslo በረንዳው ላይ ተቀምጦ ያለ
አንድ ጎልማሳ አለ።
ምሑር የሚመስል እቅደዚህ ያለ ጎበዝ
ከኬክ ቤት በራፍ ላይ ሊቀመጥ የቻለው
ምክንያቱ ምንድን ነው?
ቀኑ ቅዳሜ ነው።

የሆነች ሕፃን ልጅ
የቅዳሜ ጠዋት ፀሐይ የሚመስል
ጉንጯ ላይ ፈገግታ በደማቁ ፅፋ ባጠገቤ አለፈች
ሠላሣ ማለቂያ
አርባ መጀመሪያ . . . አካባቢ ያለች
የተጠቀለለ የታሸገ ነገር በጇ ላይ የያዘች
የሕፃኗን መንገድ እየተከተለች
ጠይም ሴት አለፈች።
ለቅድሟ ሕፃን እናቷ ነች መሰል
(ይመስለኛል መሰል)
የቤቷ ባለቤት
የልጅቷ አባት
ትንሽ አመም አርጎት ሆስፒታል ተኝቷል
ወይም . . .
የተጠቀለለው የታሸገው ነገር
የወይን የውስኪ ጠርሙስ ግን ከሆነ
ጠይም ቆንጆዋ ሴት
አንድ የተፋታችው አንድ የምትፈልገው
የሆነ ሰው አለ . . .
ትንሿን ሕፃን ልጅ የምታስተዋውቀው
እና . . .
የ'ርጅና ፍርሃቷን አብራ ምትጋራው።
አያገባኝ ነገር

ያገባኛል ብዬ ይህን ያሰብኩበት ምክንያቱ ምንድ ነው?
ያ ቀን ቅዳሜ ነው።

ይህንና ያንን
የገራ የቀኙን
ከፒያሳ መሐል እስከ ጣልያን ሠፈር . . .
አንዱን እያነሳሁ
አንዱን እየጣልኩኝ
በሐሳብ ሕንፃ ላይ አንዱ እየተሰራ አንዱ እየፈረሰ
ከልጅቷ ጋራ
የተቃጠርኩበት ሠዓቱ ደረሰ
መጣች ተገናኘን
ዮኾምያ ምሳ ቶምካ ቡናችን
የደንቡን አደረብን።
ልብሷን ሳታወልቀው ራቁቷን ሳልኳት
ዘወትር አንድ ቤት
ደንብ አይደለም ብዬ ቦሌ እንሂድ አልኳት
የተስተካከለ
ጥሩ አልጋ ያለው የማውቀው ቤት አለ።
ፒያሳን ለቀቅን . . .
ቦሌ ላይ ደረስን . . .
የቦሌ ቅዳሜ ያራዳን አይመስልም
የቦሌ ቆንጆ ሕልም ከፒያሳ ቅዥት አይስተካከልም
የቦሌ ኮረዶች
በቀለማት ብዛት ውበታም ቢመስሉም
ጣልያን ሠፈር መሐል
ፀጉር እየተሰራች ያስተዋልኳት ሴት ላይ
ጥፍሯ ላይ አይደርሱም
የቦሌ ቅዳሜ ያራዳን አይመስልም።
ቦሌን ታዘብኳትኝ
ቦሌን እርም አልኳትኝ
ቆንጆ አልጋ አለበት
ካልኩት መንገድ መሐል
አንድ የለቀሰ ድንኳን
ጎዳናውን ከድኗል።
ድንኳን ያ'ዘን ድንኳን

በ'ለተ ቅዳሜ በውበት በሕይወት ቀን
አብራኝ ያለችው ሴት
ተከተለኝ ብላ ወደ ኋላ ዞረች
እጆቿን ዘርግታ
እንድ ትንሽ ታክሲን ፒያሳ አዘዘች
ፒያሳ ደረስን
የቦሌውን ድንኳን እንዲያበረሳን ብለን
Sunshine ገሬ አልን . . . .
ሙዚቃ
ሙዚቃ
ቢራ
ውስኪ
ቢራ . . .
ጫጫታ
ዳንኪራ
ዳንኪራ
ጫጫታ
ድንኳኑን ረሳን
ውበት ባህር ገባን
የዚህ ሁሉ ደስታ የዚህ ሁሉ ሐሴት . . .
ምክንያቱ ምንድን ነው?
ቀኑ ቅዳሜ ነው።
ያውም የፒያሳ
እውነት ለመናገር . . .
የቦሌ ቅዳሜ ያራዳን አይመሥልም
የቦሌም ቆንጆ ሕልም ከፒያሳ ቅዠት አይስተካከልም።
ያም ሆነ ይህ ገና
የዚህ ሁል ዉበት ምክንያቱ ምንድን ነው?
(ቀኑ ቅዳሜ ነው።)

21-02-2004

ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር

ያሳለፍነው ሁሉ
አሁን ትዝታ 'ንጂ
ውስጡ ሕይወት የለም እያልሽ ላገሩ
ታወሪያለሽ አሉ። አሉ
(እኔ ግን ልንገርሽ)
የሁለታችን ፍቅር
ምን እንደሚመስል . . . እንዴት እንደነበር
በሦሦት ምስክር
1
አሁን በቀደም ለት
የሆነ ቦታ ላይ
ድምጻችን ከፍ አርገን የሳቅንበት ቦታ
ፒያሳ አደባባይ
ድንገት
በቀደም 'ለት
በዛ ቦታ ስሄድ
ከሰባት ወር በፊት ስቀሽ የነበረው
ያንቺ ሳቅ ተሰማኝ
መራመድ አቃተኝ።
የሚገርምሽ ነገር ያለፈ ነው ያልሽው
ትዝታ ነው ያልሽው
ፍቅርሽና ሳቅሽ
ከሰባት ወር ኋላ እንደ ወንዝ ፈሳሽ
ይሰማል ልንገርሽ።
(ታዲያ ለምንድን ነው)
የወንዝ ውሃ ሳቅሽ
ያለፈ ትዝታ ምናምን ነው ብሎ
ማንም ተራ ዘፋኝ የሚሸነግልሽ።
(ይልቅ እኔን ሥሚኝ)
ወደ ምንም ሳይሆን
ወዴትም ተመለሽ
የትም ሳትደርሺ
ጊዜን እንዳቆምነው
እንኳን ጊዜ ቀርቶ ሰዓት እንዳልሄደ

ደቂቃ እንዳልሄደ
አስረጂ ሊሆንሽ
ምስክር ሊሆንሽ
ከምንም አቅጣጫ . . . የትም ሣትመለሽ
አደባባይ መሃል
ከቡና ጠረን ጋር
እንደ ወንዝ የሚፈስ ሳቅሽን ትሰሚያለሽ።

2

ትዝ ይልሽ እንደሆን ከአንድ ዓመት በፊት
ካንቺ መኖሪያ ቤት
(የመጣሁኝ ጊዜ)
የመራራቅ ናፍቆት አስከሮን ቸኩለን
ሠማያት ለመዝለቅ ከመሬት ላይ ወድቀን
ፍቅር ሥንሠራ
ፍቅር ሥንሠራ
ፍቅር ሥንሠራ
ከሴት ወዝሽ ጋር የጡትሽ ስር ሽቶ
ሸሚዜ ላይ ቀርቶ
ሸሚዜ ላይ ቀርቶ
ምወደውን ሸሚዝ ለመልበስ እርም አልኩኝ
ለብሼው እንዳልሄድ ከበደኝ ጨነቀኝ
ያንቺን ጠረን ማጠብ . . .
ነፍስ ያማጥፋት ያህል ሐጢዓት መሰሎ ታየኝ
(የሚገርምሽ ነገር)
እስከ ዛሬ ድረስ
በመስኮቴ ዘልቆ . . . በበሬ የሚወጣው የማለዳው ነፋስ
በሽቶሽ ጠረን ነው መንደሩን የሚያብስ
ነፋስ።

3

ታስታውሽ እንደሆን
የሆነ ቅዳሜ
የሆነ ውብ ሆቴል
ደግሞም አትረሺውም . . . ፍጻሜ ምሣ ነው
ይኼ እንኳ ትዝ ይላል
እና . . .
እኔና አንቺ ብቻ

የተቀመጥንበት ወንበር ጠረጴዛው
ከዘጠኝ ወር ኋላ . . .
እዛው ቤት ዳግመኛ ተመልሼ ባየው
የሚገርምሽ ነገር
ጻፊውን ባላውቅም
ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር
የሚል ጽሁፍ ሠቅለው
ከዘጠኝ ወር ኋላ
አንድ ለብቻዬ ካንድ አንቺ ናፍቆት ጋር
ነበር ለምትይው ለሁለታችን ፍቅር
(ምስክር ሊሆኑን)
ያኔ ሁለታችን የጠጣነው ወይን
ከወይንም . . . Two Ocean
እኔ የጨለጥኩት
አንቺ ያጋመስሽው
እኛ ያስተረፍነው
እስከዛሬ ድረስ
ያስተረፍነው ማዕድ . . . ጠርሙሱና ጽዋው
በክብር ተቀምጧል
ማንም ሳያነሳው . . . ያኔ እንደነበረው
(ታዲያ ምን ማለት ነው)
ፒያሳ አደባባይ
የወንዝ ውሃ ሳቅሽ ከቡና ጠረን ጋር
ከኔ መኖሪያ ቤት . . .
የምወደው ሸሚዝ ላይ የሸቶ መዓዛሽ
ከሴት ላቦትሽ ጋር
ደግሞም
እዚያ ውብ ሆቴል ሥር
ያስተረፍነው . . . ማዕድ ጠርሙሱና ጽዋ
እንጀት ከሚበላ
ከቆንጆ ጥቅስ ጋር
"ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር።"
ነበርን እስካሁን በመሆን እያየሽ
ሣቅሽ ፈሶ ሳያልቅ
ከምወደው ሸሚዝ የሸቶ መዓዛሽ ውብ ጠረኑ ሣይለቅ
ማዕድ ሣይነሣ ጽዋው ሳይታጠብ

ሦሥቱን ምስክሮች ባይንሽ ፊት እያየሽ
(ታዲያ ለምንድን ነው)
ያሳለፍነው ሁሉ
አሁን ትዝታ 'ንጂ . . . ውስጡ ሕይወት የለም
ብለሽ ለመንደሩ ላገሩ ማውራትሽ
እውነት ለምንድን ነው?

21-02-2004

ፍርሃት

ወረቀት ዘርግቼ
ግጥም እየጻፍኩኝ ሥዕል እየሳልኩኝ
'ድሮ' እንደምታውቂኝ አለሁ እስከ ዛሬ
እርግጠኛ ልሁን
ይሕን ስታነቢ ፊትሽ ላይ ይፃፋል . . . የሆነ ዐይነት ወሬ።
የሚያሳዝን ዐይነት
የሚያስለቅስ ዐይነት
ያም ሆነ ይህ ግና የሆነ ድንጋጤ
በዚህ ጽሁፍ ምክንያት ፊትሽ ላይ ተጽፏል
ፊትሽ ላይ ይታያል።
(ይቅርታ አድርጊልኝ) . . .
በጣም ከስቀየመሽ 'ድሮ' የሚለው ቃል
ድሮ የሚለው ቦታ
ሌላ ቃል ተክተሽ ማንበብ ግን ይቻላል።

29-02-2004

## በቀደም ሜክሲኮ

በቀደም ሜክሲኮ . . .
ከሆነ ሰው ጋራ ስትመላለሺ . . .
አይኖቼ አስተዋሉሽ
ደረቅ ፈገግታዎች . . . ማድያትሽ ስር ነበር
ትንሽ ቀልብ ማጣት . . . እግሮችሽ ሥር ነበር
ሁሉንም ሰው ማየት . . .
ከዐይኖችሽ ስር ነበር
ጊዜውን ላስታውስሽ
ደም ተላብሶ ነበር ፊትሽ እንደ ጀምበር።

29-02-2004

# ከዘጠኝ ወር ኋላ

ካንቺ ጋር የሳቀው የአንቺ ጓደኛሽ
ካርታ 'ሚያጫውትሽ
ሲጋራ 'ሚላከሽ
ካንቺ ጋር የሳቀው ያ-ከንቱ ጓደኛሽ
ቢራ ቤት አገኘቼው
ላንቺ መታሰቢያ . . . .'ዘጠኝ ወር' ሚለውን ግጥሙን አነበበው
እኔ ምልሽ እቴ
እንዴት ሰው ጎልምሶ ደንቆሮ ይሆናል
ላንቺ መታሰቢያ ዘጠኝ ወር ሚለው ቃል
ግጥም ነው? ሥድብ ነው?
ወይንስ ምንድነው ሊያስታውስሽ 'ሚችል
እ . . .
የሆነች ምታምር ቆንጆ ሴት ልጅ አይደል?
ወይም. . .
ትንጨ ወፈር ያለ . . .የሆን ድንቡሽቡሽ ሕጻን ልጅን አይደል
ታድያ. . .
ያ-ከንቱ ጓደኛሽ ምን ልሁን ብሎ ነው
ወይስ የልማዱን አሽሙር ማድረሱ ነው
ዘጠኝ ወር
ዘጠኝ ወር . . .ዘጠኝ ወር የሚለው
አብሶ ለሴት ልጅ . . . ድንቁም ግጥም ጽፏል
ዘጠኝ ወር ለሴት ልጅ . . .
ዘልዓለም መሆኑን 'ምን' ሰው ይነግረዋል

29-02-2004

## እልሀ

ለጥበብ ቀዳሚው
ጥበብ መጀመሪያው ሲጋራ ማጤሥ ነው
እያለ ሚያወራው
ያ ከንቱ ወዳጅሽ
እንዲህ ስላወራሽ . . . ሰቀሽ ነበር አሉ
ያውም . . .
እጅሽን ዘርግተሽ
እግርሽን እንስተሽ
ይሁን
ይሁን
ይሁን
ግቂ ችግር የለም
ግን
እኔ የምናደድ የምበሽቅ መስሎሽ
እንዴት ከ'ማንም' ጋር የትም ትሆኛለሽ።

29-02-2004

'ምንድን'

እኔ 'ምንም' ሆኜ - እርሱ 'የትም' ሲሆን
አንተ ማን ልትባል?
ብለሽ ጠይቀሻል።
የሚገርምሽ ነገር . . .
ያ . . . አሪፍ ጥያቄሽ ከጆሮዬ ደርሷል
ረስተሽው እንጂ . . .
ለዛችን ፍቅራችን እንደተጀመረ
ሴትነት ውበትሽ አቦል ቡና እያለ - ነግሬሽ ነበረ።
አልጋሽ ላይ ቁጭ ብዬ . . .
ካሰር ዓመት በፊት ትዝ ይልሻል አይደል?
የ'ምንም' ጓደኛ . . . 'ምንድን' እንደሚባል።

29-02-2004

ሁለተኛ ስሜን
ብታነሳው ብለሽ . . . ብትጽፈው ብለሽ
ከኔ ጋር ለማውራት
ፊቴ ተቀምጠሻል . . . ቁጭ ብያለሁ ፊትሽ
እሺ . . .
ምን ብዬ ሰደብኩሽ
ማን ብዬ ጠርቼ በከፋ አነሳሁሽ
አባከሽን __________ ሆይ
ከነበር ከምንም . . . የትኛው ነው ስምሽ?

29-02-2004

## አንፃር

የማውቀው ሦሥት ዓመት
ምን ይሉት ፈሊጥ ነው
ካሰር ዓመት በፊት እያሉ ላገኙ በመጽሃፍ ማውሬት
ብለሽኛል አሉ። . . .
አለች ብለውኛል
እኒያ ጓደኞችሽ በማኪያቶ ግብዣ ሚደለሉ ሁሉ
ሚደልሉሽ ሁሉ
በርግጥ እውነት አለሽ . . .
የሁለታችን ፍቅር ረዥሙ ዕድሜ ሦሥት ዓመት ብቻ ነው
ለምን የሁለታችን? ያብዛኛው እንዲያ ነው
ግን
የወንዱ ይቅርና
በሴት አቆጣጠር ሦሥት ዓመት ሥንት ነው?

29 - 02 - 2004

ነበር

በቀደም ቦሌ ላይ
አንቺ . . . አገሊት . . . አንትና
አንቺ ማለት ምንም
ከዘመናት በፊት
በምን ዐይኖች ስር ታይታ የነበረች
ታይታም የተፈታች
ነበር የምትባል
ታላቋ ምርጧ ሕልም
በኔነቴ ሜዳ ትጫወቱ ነበር
ነበር እያላችሁ
በነበር ደምቃችሁ
ምንም . . . ማንም . . .የትም . . . ሦሥታችሁ ሆናችሁ

29-02-2004

አንባር ፪

ታሪኩ ደስ የሚል
ገጹ አርጀት ያለ
የሆነ መጽሃፍ መዳፌ ላይ አለ
መጽሃፉ ሳይሆን
የመጽሃፉ ሽፋን
ያንቺን ሕይወት መስሎኝ ዕንባዬ ጠብ አለ።

ተነቦ ያለቀ ምርጥ አሮጌ መጽሃፍ
ማንም በተውሶ
ሲገልጠው የኖረ ምርጥ አሮጌ መጽሃፍ
ሽፋኑ ያለቀ
ያለቀ ሽፋኑ በጥቁር ፕላስተር የተለጣጠፈ
በ'ማንም' መዳፍ ላይ
የትም ሲገላለጥ ሽፋኑ ያደፈ
ታሪኩ ደስ የሚል
ገጹ አርጀት ያለ
የሆነ መጽሃፍ መዳፌ ላይ አለ።
እና . . .
ይህንን መጽሃፍ ባይኖቼ ሳስተውል
ምስልሽ ይመስለኛል . . .

29-02-2004

# አንባር ፫

እስከ ዛሬ ድረስ
የዛን ጊዜው ክብሬ
የነበረው ፍቅሬ
በነበር ቢቀርም . . . እንደነበር አለ
እውነት ከኔ በቀር
'ነበር' ያንቺ መንታ መሆኑን የሚያውቅ ከቶ ምን ሰው አለ?

29-02-2004

ዛሬ

ዛሬ ደብሮኛል
ግን
የልደቴ ቀን ነው
ጊዜ እንዴት ይበራል
ሕልም እንዴት ይረሳል
ማኪያቶ እየጠጣሁ እያስታወስኩሽ ነው
ያንዲት ሴትን ዕድሜ
ጊዜ ተሸክሞት . . . ጊዜ ላይ ሲጥለው
ምንድን ነው ሚመስለው?
እያልኩ . . .
ሴቶችን ባንቺ ውስጥ እያሰብኳቸው ነው!!
መቼም የምትባል ጎደኛሽን ሣይቀር
ውስኪ ቤት ያለቀ
በየወንዱ እልጋ የተለቃለቀ ውበትሽን ሣይቀር
በዘመናት ድምር
አሰብኩት አሰብኩሽ
አሰብኩሽ
አሰብኩሽ
ሐጢአቴ ትዝ አለኝ
በደሌ ታወሰኝ
በጣም . . . እጅግ በጣም እንደአስቀየምኩሽ
በደሌ ታወሰኝ
ከመቼም ተኝቼ ምንም ዘልዓለሜን
ምንም ሁልጊዜዬን እንደሰበርኳትኝ።

29-02-2004

## አላዋቂ ሳሚ

ያንን ከንቱ ልጅን ባከሽ አረፍ በይው
ማንም የሞላውን
የየትም ጎደኛን።

-

እውነቱን ልንገርሽ
ማንም ስለ-ምንም ምንም ሊል አይችልም
ምን እኔ እያለሁ 'ምንም' አይባልም
ግና ምን አውጥቶ
ምን ሊል ግን ይችላል
ምን' ፍጥረት እያለ . . . ምንም እንዳይባል
ይሔ ዲስኩረኛ
ማንም ግን ይገርማል
ምክንያቱም
የገዛ ራሱን ስም ከምን ጋር ያጋባል . . .
እባክሽ ተው በይው።

29-02-2004

ፍርሃት ፪

ሁሌም መሽት ሲል አስታውስሻለሁ
እንዴት ናት? እላለሁ።
ምንም ወዳጄ ሆይ . . .
የቤትሽ ፀጥታ ዛሬም እንደያኔው
እንደዚያን ጊዜው ነው?
እኔ ምልሽ ምንም
ቤትሽ አመሻሽ ላይ ቴፕሽን አጥፍተሽ
መብራትሽን አጥፍተሽ
የራስጌሽን አምፖል ፊትሽ ላይ አብርተሽ
አረፍ ስትዪ
ያ . . .
ግድግዳው ልብ ላይ የሰቀልሽው ሰዓት
ትክ
ትክ
ትክ . . . ትክ እያለ ሌሊት ሲጮህብሽ
እንዴት አድርጎ ነው እንቅልፍ የሚወስድሽ።

29-02-2004

## አቦል

መቼም ታውቂዋለሽ?
ዛሬ-የዓውዳመት ዋዜማ እንደሆነ
በየትኛውም ቤት
መሬት ወለሉ ላይ አረንጓዴ ለምለም እንደተበተነ
ቡና እስከሚጠራ
አቦል እስኪጣራ
ነበረ
ነበረ
አረንጓደው ለምለም የትኛውም ወለል ተከብሮ የኖረ።
ቡና እስከሚጠራ
አቦል እስኪጣራ። . . .

29-02-2004

፪ ጊዜ ፫

1 . . .
ጠዋት በማለዳ
ተነስተሽ ነው እሉ
ለማይረባ ባልሽ ሽንኩርት የምትከትፊው
ያኔ ከኔ ጋራ በፍቅር ስንኖር
ሕልምሽ ይሔ ነበር? . . .
2 . . .
ደግሞም
ቁርስ የበላችሁበት
ሠሐን ሳይታጠብ
ለማይረባ ባሏ . . . ምሳውን ለመስራት ጉድጉድ ትላለች
እያሉ ያሙሻል
"በናትሽ ምንም ሆይ"
ያኔ ከኔ ጋራ በፍቅር ሥንኖር
ሕልምሽ ይሔ ነበር?
3 . . .
ዚላ ያለው ማግባት
ገንዘብ ያለው ማግባት
ፍቅርን አያመጣም እያለች ሁል ጊዜ ታወራለች እሉ
ማኪያቶ ሊጠጡ
ጠዋት ሚደውሉት ጓደኞችሽ ሁሉ
ትላለች ይላሉ . . .
ታዲያ ምን ያደርጋል
ሦሥት ዐይነት ሥህተት ሕይወተሽ ውስጥ ገብቷል
1
ትላንት አልሮብሻል
2
ዛሬ መሽቶብሻል
3
ባለፈብሽ ትላንት በመሸብሽ ዛሬ ነገ ያስፈራሻል?
ምንም ወዳጄ ሆይ
ከኔ ከ'ምን' በቀር የማይረባው ባልሽ ይሕን ያውቅልሻል።

29-02-2004

## የአልቦ አሻራዎች

ምንም ወዳጄ ሆይ
ያ ከንቱነት ባልሽ
ውድቀት እስከሚሆን ሰርክ እየሰከረ
እንደሚያስቸግርሽ
በቀደም Tomocca ነግረሽኝ ነበረ።
ነግሬሽ ነበረ
ለምኜሽ ነበረ
ግን . . .
ገንዘብና ቤቱን ልብሽ አከበረ
ፍቅር ማደሪያ አጣ 'ወዴትም' ተጓዘ ወደ አልቦ በረረ
ያልኩሽ ግን አልቀረም
ከንቱነት ከንቱ ነው አድርጎሽ ያስቀረ።

30-02-2004

ከብዙ ገጽ አንዱ

ምንም ወዳጄ ሆይ
ሁሌም ባንድ ነገር አንቺን እስባለሁ
አንቺን አከብራለሁ
እርሱም . . .
ምንም ጨካኝ ብትሆን
ባታዝንልኝ ኖሮ . . . 'ምን' ለምባል ፍጡር
በፍለጋ እንዳብድ
ስሜ 'ምንም' ብላ አትነግረኝም ነበር።
ብዬ . . .
የሆነ ስፍራ ላይ
የጻፍኩትን ግጥም ወረቀት ላይ ልጽፍ ሐሳቡ መጥቶልኝ
መጻፍ ልጀምር ስል ሃሳቡ ጠፋብኝ።
ልክ እንዳንቺ

29-02-2004

## ሕልም

ትላንትና በ'ልሜ
ከንቺ ጓደኛ ቤት ከመቼም አልጋ ላይ
አንቺ ተኝተሻል . . .
ጥልቅ ዕንቅልፍ ይዞሻል . . .
-
የሚገርምሽ ነገር . . .
እኔ በተኛሁት
ተኝቼ በማየው በሕልሜ መካከል
ተኝቼ - ተኝተሽ
ጥላሽን ታያለሽ
በገዛ እንቅልፌ . . . በሕልሜ ተኝተሽ
የኔን የሚመስል ሕልም አንቺም ታያለሽ
ተኝተሽ - ተኝቼ
ጥላዬን ታያለሽ።
-
ሕልሜን ሳልጨርሰው
ጥላዬ ካለበት
ጥላሽ ከአለበት - ከ'ንቅልፍ ዐለም ሕልሜ በድንገት ነቃሁኝ
በድንገት ስነቃ . . .
ከ'ንቅልፌ ከሕልሜ የተረፈኝ ነገር
ምንም ምንም ላይሆን ምንም ብቻ ነበር።
(ሕይወት እንደዚህ ናት)

29-02-2004

በረከ

የበቀደም ለታው
ላመት ባ'ል ዋዜማ
ተበትኗል ያልኩሽ አረንጓዴው ቅጠል (ወለል)
ዛሬ እንዴት ያስጠላል?
ለምለም የነበረው የሣር ድርቆሽ መስሏል
አረንጓዴ ያልነው ግራጫ ገጽ ይዟል
ምንም ፍቅረኛዬ
ባክሽ ላስቸግርሽ
ፍርሃት ልቤ ገብቶ ያስጨንቀኝ ይዟል
ጽልመት ፀጉሬ መሐል ትንሽ ጥጥ ይታያል
ምንም ናፍቆቴ ሆይ
ባክሽ ላስቸግርሽ - ግድግዳ ላይ ያለው ሠዓትሽ ስንት ይላል?

29-02-2004

10:30

አመሰግናለሁ . . .
'ሚገርም ነገር ነው ጊዜ እንዴት ይሮጣል?
አስር ሰዓት ተኩል?
ፀሐይ ከሙቀቷ በረድ ብላለች
ምድር ከፍጥነቷ ትንሽ ታግባለች . . .
ቢሆንም
ቢሆንም
አስር ሰዓት ተኩል?
የሚገርም ነገር . . . ጊዜ እንዴት ይሮጣል?
እኔ ምልሽ ምንም . . .
መቼ ለታ ነበር
ስንት ሰዓት ነበር . . .
በቀደም አልነበር
ኩኩሉ ጨዋታ ዛፍ ስር ስንጀምር
አርባ እስከምትቆጥሪ . . . እኔ ከቅጠል ስር ሥደበቅ የነበር
በቀደም አልነበር . . . እኔ ከጉድጓድ ስር ስከለል የነበር
አስር ሰዓት ተኩል?
ጊዜ እንዴት ይሮጣል?!

29-02-2004

## የከረምት ሸሽት

ዕሁድ . . .
በተስኪያን ስመሽ ስትመለሺ ነው . . .
ጥበብ ቀሚስ ለብሰሽ መንገድ ላይ ያየሁሽ
እንዴት ያምርብሻል?
ባትወልጂም ባትከብጂም እናት ግን መስለሻል፡፡
በቀኝ እጅሽ በኩል ቁጤማ ይዘሻል
የዛን ቀኑ በዓል መስቀል ይመስለኛል
እንደውም ያን ጊዜ . . .
ከንቱነት ያንቺ ባል
ትንሽ አመም አርጎት ሆስፒታል ተኝቷል
ብለው ነገረውኛል፡፡

29-02-2004

ገጽ 31

ለኔ መታሰቢያ . . .
የሚሆን ውብ ግጥም ጻፍልኝ ብለሻል
ታድያ ምን ያንሰሻል
ይኸው
ይኸው ይኼኛው ገጽ
ላንቺ መታሰቢያ እንዲሆን ተፈቅዷል
ምክንያቱም ባከነሻል
ፍቅሬን ረግጠሻል . . .
ያላንዳች ተግባር ያላንዳች ፈጠራ ጊዜሽን በልተሻል
ሥለዚህ . . .
ይህን ግጥም ማይሆን
ይህ ግጥም ያለበት የዚህ ገጽ ቁጥር
ዕድሜሽ ትዝ እንዲልሽ
የልደት ሥጦታ ተበርክቶልሻል . . . በፍቅር በክብር።

27-02-2004

አሑን

አሑን ከአሑን ጋራ
እስከ አሑን ድረስ አብረን ቆመን ነበር
ለዚያውም እዚህ ጋር

ስስ ጊዜ-ከንፈሯን . . . ቸኩዬ እየሳምኩት
ቀን የፀሐይ ጥርሷን
ሌሊት ልስልስ ጸጉሯን
ከረምትና ጸደይ ውብ መንታ ጡቶቿን
የአሁንን
አሁን . . .
አሁን እየሳምኩት
ምንም የሆነውን የነበርን ፍቅር ዳግም ላለማየት
አሁን ነበር ሆኖ ለአለመጸጸት
ነበር ምንም ሆና ደግሜ እንዳላያት . . .
አሁን ከአሁን ጋር
እስከ አሁን ድረስ አብረን ቆመን ነበር
እዚህ ጋር
በፍቅር።

29-02-2004

እውነት ወደ ኋላ

ገንዘብ ካለው ጋራ
ፍቅር አይኖርም ወይ ብለሽ ጠይቀሻል
እኔ ያንቺን እንጂ
የሌላን አላልኩም እጅግ ተሳስተሻል
አይኖርም አላልኩም . . . አይጠፋም ይኖራል
ይኖራል
ይኖራል
ግን? . . .
ከባለሐብት ጋር
ተፋቅራ 'ምናያት የቷም አይነት እንስት . . .
'ምን' ትሁንም ፡ምንም'
የሕይወት ታሪኳን ወደ ኋላ ሄደን . . . ጥቂት ብንገመግም
አንድ ቡና ለሁለት . . .
አብራ የጠጣችው አንድ አፍቃሪ አታጣም።

29-02-2004

## ነበርን ወደፊት

የበእሉ ለታ
ሲበተን ያየነው አረንጓዴው ሁሉ
በበእሉ ማግበት
ሲጠረግ ያየነው ገራጫው ሳር ሁሉ
ያንቺን ወጣትነት ይወክላል እሉ።
ታድያ . . .
እኔ ከአሁን ጋራ በተኛሁኝ ቁጥር
አሁን አረንጓዴን በሣምኳትኝ ቁጥር
አንዳንዴ በመሀል ትዝ የሚለኝ ነገር
ነበር የሚባለው የሁለታችን ፍቅር ነበር።
ነበር
ነበር ባሁን ፍቅር ምንም ሆኖ ባይቀር?
ነበር።

29-02-2004

## ነበር ወደ ኋላ

በቀደም ከባልሽ . . .
መጣላታችሁን ጎረቤት ነገረኝ
የጸቡም ምክንያት
ግድግዳ ላይ ያለው
ያንቺ ቆንጆ ፎቶ መሆኑን ሰማሁኝ
እኔ ምልሽ ምንም?
ይሄ ከንቱ ባልሽ . . . ምን ልሁን ብሎ ነው
ያኔ በዚህ ጊዜ
ከማን ጋር ነበርሽ እያለ ሚጣላው?
ምን ልሁን ብሎ ነው
ወይስ ከኔ ጋራ
የተጣላሽበት ትልቁን ምክንያት
ምስጢሩን አውቆ ነው?
የመቼም ባል ማንም አብሮሽ እንደተኛ . . . ሐበሻ ሹክ አለው?
ታድያ ለምንድን ነው . . .
ነበርን እንስቶ . . . ምንምን ምን-ጊዜም ሲያስለቅስ 'ሚኖረው?
እኮ ለምንድን ነው?

29-02-2004

## ከትላንት ወዲያ

ምንም ሆይ . . .
በትላንት ጥፋት ተጸጽተን
ያምናን ጸሎት ደግመን
በተስፋ ተጠምቀን . . . ዛሬን እንቆርባለን
የሚያሳዝነን ነገር . . .
ዛሬን በናልፋት ግን
ነገ ዛሬ ሲሆን
ምንም ደስ ይበልሽ . . . ከትላንት ወዲያ ነን።

መስታወት

ከንቱነት በሽታው
ብሶበታል ብለው ብ'ዞች ያወራሉ
አልጋ ላይ ሳይወድቅ
ታሞ እንደነበረ የማያውቁ ሁሉ
ደግሞም . . .
የበሽታው አይነት ተስፋ መቁረጡ ነው እያሉ ያማሉ
የከንቱ ጓደኞች
'ማንም' ና 'የትም' ሆነው እንደነበር እንዳላዩ ሁሉ
ይህን ሁሉ ሐሜት
ይህን ሁሉ ወሬ . . . የሕይወት ጉጉቶች ለምን ያወራሉ?
ብትዩ? ወይም ደግሞ ቢሉ?
በከንቱ ማንነት ራሳቸው አሉ . . .

29-02-2004

## መዝሙር ለአያቶች

ምንም ወዳጄ ሆይ
አሁን በዚህ ዘመን
'የኔ-አያት' ብለው . . . የሚያወሩ ልጆች በጆሮሽ ሰምተሻል?
ባይኖችሽ አይተሻል?
(ምናልባት ጥቂቶች)
በዚህ ዘመን እንደሁ . . .
ሃምሳ ሺ ቢወልዱ። መቶ ሺ ቢያፈሩ
ወላጅነት ከንቱ . . .
'ማን' 'ምንነታቸው' ብዙም አይሰማም በልጅ ልጅ ሲወሩ
የሚገርምሽ ነገር
ከልጆች በስተቀር _
የልጅ ልጆች ማየት? የጥቂቶች ተስፋ የጥቂት ዕድል ነው
በብዙዎች ገና . . .
ያያቶች ማንነት ከፎቷቸው በቀር ቅዥት ነው ምሳሌው
እናም . . .
አንዳንዴ ሳስበው
ከ'ንዲህ ዓይነት ልጆች
እንዳንቺ አለመውለድ እድገ መታደል ነው
ብዙ ነው ቡራኬው።
ምክንያቱም . . .
አንቺም ብትወልጂ ያንቺኑ ቢጤ ነው።

29-02-2004

ገጽ 39

ገጽ 31 መታሠቢያ ብዬ
ለሆነ ልደትሽ ሰጥቼሽ ነበረ
አንቺ ግን ተናደድሽ
አንጀትሽ አረረ ቅስምሽ ተሰበረ
እውነቱን ልንገርሽ
ጺቤ ገራገር ነው አዝኜልሽ ነበር
ሴትነትሽ 'ንጂ . . .
የውነት ዕድሜሽማ
የዚህ ግጥም ርዕስ
ወይም ወይም ደግሞ . . . የዚህ ገጽ ቁጥር
ነበር።
እና ባዘንኩልሽ . . .
ምን ልሁን ብለሽ ነው የኔን ስም ማጥፋትሽ
እንደውም ልንገርሽ
እጅግ በጣም በጣም እድለኛ ሴት ነሽ . . .
ሌላው ሌላው ቢቀር
ከንቱነትሽ እንኳ ሕያው ሆኖ እንዲኖር
ግጥም ተጻፈብሽ
አስራ ዘጠኝ መስመር።

29-02-2004

ላርባ አንድ ፊሪ

ገጽ 31
ገጽ 39
ገጽ ___ እና ላርባ አንድ ፊሪ
ያስጠላኛል ብለሽ የተናገርሽኝ ሴት
ማለዳ ገጥሜን
አንበሽ ስትጨርሽ የዛን ዕለት ምሽት
የት ነበርሽ? . . .
ቅራሪ ውበትሽን በቀለም ሽንገለሽ
ገጥሜ ያወራሽን እውነት የልብ ሐቁን በሥድብ ለውሰሽ
የዛን ዕለት ምሽት የት ነበር ያየሁሽ! . . .
የት ነበር
የት ነበር?
የዳንስ ቤት ዕውቀት ስልጣኔ መስሎሽ
የመጠጥ ስም ዕውቀት ምሁርነት አ'ርገሽ
በገጥሜ ተናደሽ
የዛን ዕለት ምሽት ውስኪ ቤት አልነበርሽ።
እሺ - ታዲያ እኔ
መደለል አለብኝ
መሽንገል አለብኝ
ታዲያ ምን ማለት ነው
ጠዋት Caffteria መጽሃፌን ይዘሽ
በጹፌ ተናደሽ
ውስኪ ቤት ስትገቢ
ድሮም እኔ ገጥም አልወድም ማለትሽ
የጎዳሽኝ መስሎሽ
የማላውቅሽ ሙቺ
የማታውቂኝ ሙቺ . . . ሥጨኝ መዳፍሽን
በማርያም . . . በማርያም . . .
አንቺ እንደሆነ ጥንትም
ከዘመን ጋር 'ንጂ ከኔ ጸብ የለሽም።

29-02-2004

ገጽ ከዚህ በፊት

ይህን መጽሐፍ ገልጠሽ
እዚህ ድረስ አይተሽ
መቼ ለታ ነበር? እዚህ ጋር ያቆምሽው
'ሌላ ጊዜ' ብለሽ
ሥራ እንደበዛበት ጊዜ እንደሌለው.ሰው።
(ምልከት እንዲሆን)
ጠርዙን አጠፍ አ'ርገሽ
ከንፈርሽን ነክሰሽ
የደከመሽ መስለሽ _
ግን!
ወዳጄ 'ምንም' ሆይ በ'ውነት' በናትሽ ሞት
የመጽሃፉን ጠርዝ . . .
አጥፈሽ ማስቀመጥሽ ምልከት ሆኖሻል?
ወይስ
እርጅና እንደባተ መርዶ በመንገሩ በጣም ተናደሻል
አይደል? ______

29-02-2004

## የበር ጩኸቶች

የቤት ሰራተኛሽ
ሥራ ጨርሳለች . . . ግን
ሥራ ስ' ተሻታል
እ' ሷ ግን
እንዳስለመድሻት ካንቺ ጋራ ማውራት 'ምትፈልግ ይመስላል
ደግሞም . . .
አንቺና ከንቱነት የምታስተምሩት
ትንሹን ሕፃን ልጅ ሳሙና እንዲገዛ ከሱቅ ልከሽዋል
ሱቆች ተዘግተዋል።
-
አንቺ
ከመኝታ ቤትሽ ብቻሽን ተቀምጠሽ ወይም ጋደም ብለሽ
ተቅበጠበጪለሽ
ትበሰጫጪለሽ
አየሽ
ካለፈ በኋላ የትኛውም ነገር እንዲህ ያናነድዳል
በጊዜው ካልሆነ
ሁሉም ያለጊዜው ይቀፋል ያስጠላል
-
ሳሙናውን ይዞ ሕፃኑ ልጅ መጥቷል
ሳሎን መሃል ቆሟል
ከበራፍሽ ገና አንድ የሆነ ድምጽ በርቀት ይሰማል . . .
ተነሽ ከመኝታሽ ደጃፍሽ ይመታል
ይንኳኳል
ይንኳኳል ደጃፍሽ ይንኳኳል
ከንቱነት በሩ ላይ በጣም ሰክሮ ቆሟል
ሂጂ ክፈቺለት . . .

29-02-2004

## መስታወት ፪

እንዳንዴ በበርሽ አለፍ ገደም ስል
ጀምበር ዝቅ ስትል
እሳትሽን ለኩሰሽ
እሳቱ አጠገብ እግሮችሽን ከፍተሽ
መጽሃፍ ነገር ገልጠሽ . . . ብዙ መተከዝሽ ከሩቅ ይታየኛል
ከንቱነት ባልሽም ብዙ ማምሸት ይዟል፡፡
መንደርተኛሽ ግና
ውስኪ ቤት ለቀረ
በየወንዱ እልጋ ለተመነዘረ - ላንቺ 'ነበር' ውበት ምን ብሎ ያወራል?
እርሷን የተረፋት
ግድግዳ ላይ ያለው የወጣትነቷ ፎቶዋ ነው ይላል . . .
ፎቶሽ አጠገብ ግን . . . ሠዓቱ ይጮኻል፡፡
ይልቅ እርሱን ሰሚው
ጎረቤቱን ተደው
ደግሞ ለዚህ አገር ጎረቤትና ሰው፡፡

29-02-2004

## በመታየት ማየት

ማለዳ ማለዳ
ሸጋ ልጅ ማለዳ . . . በሚል ዝፈን ፈንታ
አሁን ግን ማለዳ
ይሰማዋል አሉ ልብሽን ቅሬታ
ማለዳ ፀጉርሽ ሊበጠር ሲጀመር
ከማበጠር ይልቅ . . .
ለምዶብሻል አሉ ፀጉርሽን መቁጠር
የማለዳ ከፋት . . .
አንቺ ሥትቆሚ መስታወት ፊት ለፊት
እግዚአብሔር ከሠማይ
ይነግርሻል አሉ የ' ድሜሽን ስንትነት
መዳፍሽ ላይ ባሉት በፀጉሮችሽ ንጣት . . .

29-02-2004

## ከ እኔ ለ እኔ

ምንም ወዳጂ ሆይ . . . .
ምሽት
ጀምበር ጥልቅ ስትል
ምድር ዝም ስትል
በጊዜ ፈጣን ጣት ፀጉርሽን መዞ
ፀጉርሽ ጥቁረት መሐል
ነጩን ሲያስተውል
በምን ያጽናናሻል ከንቱነት ያንቺ ባል
ይፈራል?
ይሰጋል?
ከመጠጥ ይደግማል? . . . ባ'ልኮል ይደበቃል?
ወይስ . . .
አብረን በአንድነት እንሸብታለን ብሎ ያፅናናሻል
እንዲህ ሲልሽ ደግሞ
ልብሽን ያመዋል
'እኔ' ትዝ ይልሻል . . .
ፍርስራሹ ቃልሽ ነፍስ ይዞ ይቆማል
ምክንያት
አብረን በአንድነት እንሸብታለን የሚል ያንቺ ዕሁፍ 'እኔ' እጅ ይገኛል።

29-02-2004

፩ ጊዜ ፫

አየሽው አይደለ
ያለ ፍቅር ትዳር እንዴት እንደሚመር
ያኔ ብቸኝነት በስንት ጣዕሙ ? . . .

አየሽው አይደለ
ያለፍቅር ገንዘብ
ከማይወዱት ጋራ ትልቅ ቤት መሰብሰብ
እንዴት እንዲያሳሰብ . . .
እንዴት እንደሚጠብ?

ታድያ ምን ያደርጋል
ካንቺ ብዙ ገንዘብ ካንቺ ሠራ ከፍል
የኔ ቤት ይሞቃል
የኔ ቤት ተውቧል
ይልቅስ ልንገርሽ
ያለፈውን እርሺው ሕይወት ተጀምሯል
ጠባብ ከነበረው
ከአንድ ከፍል ቤቴ አዲስ ሴት ገብታለች አሁን የምትባል።

29 - 02 - 2004

## ግለ ታሪክ

ያን አሮጌ መጽሃፍ . . .
በሁለት መዳፎችሽ ዛሬም ይዘሽዋል
ትንሽ መሽት ሲል ______
ሳሎንሽ መካከል
ጋቢ ደረብ አርገሽ መቀመጥ ለምደሻል።
እና ግን ዘወትር
'ምታስቢው ነገር
ሌላ ምንም አይደል - 'ያኔን' ብቻ ሆኗል
ያኔ መሽት ሲል . . .
ልብስሽን ቀይረሽ
ጡቶችሽ መካከል ሽቶሽን ረጭተሽ
መስታወት ፊት ቆመሽ
ዳሌሽን እያየሽ
አንቺው ካንቺው ጋራ ባንቺው ፍቅር ወድቀሽ
ያኔ መሽት ሲል . . .
ያኔ
ያኔ . . . ያኔ . . .
በርግጥ አውቃለሁኝ
ያኔ ከነበረሽ ቁም ነገር መካከል
ፍንው ዛሬ አሁን
ጋቢ ደረብ አርገሽ ከሳሎንሽ መሃል
የምታስተውይው
ከ'ጅሽ የማይጠፋው
የገዛ ታሪክሽ ይህ አሮጌ መጽሐፍ እርሱ ብቻ ሆኗል።

29-02-2004

መጠሪያ ለ ___________

ጊዜያችን ነጎደ
ወጣትነታችን እሳቱ አመደ።
ይህንና ያንን እያስተናገደ
ያንቺም ዉብ ሴትነት ጊዜው ረፈደ።
በጣም ረፈደ።
ያራት ሰዓት ፀሐይ ትመስይ ነበረ
እንደ ትኩስ ቡና ትፋጂ ነበረ
ጡት ዳሌና ባትሽ እሳት እንዳልሆነ
እንዴት ጊዜው ፈጥኖ አሁን ነበር ሆነ።
ምንም ሆይ አባክሽ
አባክሽ
አባክሽ
ከ'ንግዲህ በኋላ
<u>ቀዝቃዛ አቦል ሴት የሚል ስም ላውጣልሽ።</u>

29-02-2004

## ድንጋይ በድንጋይ ላይ

ክትፎ የሰለቸው . . .
አፈር ከጋጠው ጋር ተቃቅፎ ተኝቷል
አፈር እንደነበር አፈሩን ቅሞታል
ያ ሁሉ ግፍ ግና
ለምን እንደሆነ ምስጢሩ ይጠፋል_____

ያም ነፍሰ ገዳዩ
ዛሬ ከሟቹ ጎን አጥንቱ ይታያል
አጥንት ለመጋጥ
ሰው እንዳልገደለ ዛሬ አጥንት ሆኗል
ያ ሁሉ ግፍ ግና
ለምን? . . . እንደሆነ ምስጢሩ ይጠፋል_____
ታድያ
ይሄ ሁሉ ውሸት ይሄ ሁሉ ተንኮል
ይሄ ሁሉ ሴራ
ይሄ ሁሉ ጉራ
ይህ ሁሉ መባላት . . . ይህ ሁሉ ማባላት . . .
ዕድሜው እንደሆነ ከሰባ ከፍ ላይል
ግን?
ለምን . . . ግን? . . . ለምን . . .
ለምን?
ለምን?
ለምን?
ታድያ _______
የሚገርምሽ ነገር
እጅግ የሚያበሽቀው እጅግ የሚያነደው
ይሄ የተጻፈው
ባልሽ ከተኛበት ድንጋይ ዐናት ላይ ነው።

29 - 02 - 2004

ቀጥሎ ላንቺ

ባዶ ገፅ ላንቺ
መታሰቢያ ይሁን
የሚል ስጦታዬን እምቢየው ብለሻል
ታድያ ምን ይሻላል? . . .
ከዚህ ገጽ ቀጥሎ ሚገኘውን ጽሑፍ
ላንቺ ባበረከት እንዴት ይመስልሻል
ለኔ ችግር የለም
ያም ሆነ ይኼኛው ሁለቱም አንድ ነው
ለንዳንቺ አይነቱ ለብዙው ተራ ሕዝብ ችግር የሚሆነው
ሥተት የሚሆነው
ስንቅፋት የሆነው
አንዱን ሳይጨርሱ ወዳንዱ ማለፍ ነው . . .
ዝግ ብለሽ አንብቢው ከኔ ለአንቺ ነው።

29-02-2004

## ላንቺ

ቅጠሎች ታውቂያለሽ
ቅጠል
ለምለም ቅጠል
ከግንድ የነበሩ
ንጹህ አረንጓዴ ሆነው የነበሩ
ውብ አበባ ሆነው ተፈጥሮን ያበሩ
ቅጠሎች ታውቂያለሽ?
ቅጠል
ለምለም ቅጠል።
(እነዚያ ቅጠሎች) . . .
ግንድ ላይ እያሉ አንቺን ይመስላሉ
ለምልመው እያሉ አንቺን ያከላሉ
'ርጥብ ፀጌ እያሉ ካንቺ እኩል ነበሩ
በነፋስ አለንጋ ሳይሰባበሩ
ለምለሞች ነበሩ።

ቅጠሎች አይተሻል?
በነፋሳት ንዴት ከግንድ የወደቁ
ወድቀው የደረቁ
ባ'ላፊ አግዳሚው እግር የደቀቁ
ቅጠሎች አይተሻል
አበቦች አይተሻል
ማንን ይመስላሉ ምንን ያወራሉ?
የእርጅናን ስጋት ለማን ይነግራሉ? . . . .
ውበት አልነበሩ
ለምለም አልነበሩ
ቅጠል አልነበሩ
ከጊዜ ዋርካ ላይ ተገፍተው ሳይወድቁ ሣይሰባበሩ
እንዳንቺ አልነበሩ።
የሚገርምሽ ነገር
የጊዜ ተአምር . . .
ቅጠሎች ከጣለው
ታላቁ ግንድ ላይ
አዳዲስ ቅጠሎች ማበብ ጀምረዋል

ቅጠል የሚረግጥ
አረንጓዴ 'ማይወድ
አላፊ አግዳሚው ባ' ይኑ ያሻቸዋል
ከግንዱ ስር ካሉት
ደረቅ ቅጠሎች ላይ
ሁለት ፍቅረኛሞች ተኝተውበታል።
መሬት ላይ የተኙት
ቅጠል ላይ የተኙት ሁለቱ ፍቅረኞች
እርጋፊ ቅጠል
ከመሬት አንስተው ባ' ውራ ጣት ሲሰብሩ
የጊዜን ምንነት
ልብ ባለማለቱ ካንቺ እኩል ነበሩ።
ምንም እንዳይገርምሽ።

ማንም'ና ምንም

ከስንት ዓመት ኋላ . . .
ሮብ ረፋድ ላይ . . . ቲ-ሩም በረንዳ ላይ
ማንምን እየሆት ከነሁሉም ጋራ . . .
<u>አፕሬቲቭ</u> አዘ
አብሮ አደጌ ብሎ የሞተው ባልሽን 'ከንቱን' እያወራ
ትንሽ ከትከሻው ማጎንበስ ጀምሯል
ፀጉሩ በጠቅላላ ነጭ ጥጥ ይመስላል . . .
አብዝቶ ያጨሳል።
እኔ 'ምልሽ ምንም
አንቺም ያኔ ድሮ ፈረንሳይ እያለሽ
እዚህ አገር? ብለሽ
ከዚህ አገር ወ'ተሽ
ከዚህ አገር ሳይሆን ከባህል ከሥርዐት ከወግሽ ተጣልተሽ
ፈረንሳይ ጎዳና መንገድ ዳር ተቀምጠሽ
እንደው ወጉ 'እንዳይቀር መጻፍ ቢጤ ገልጠሽ
አጭር ቀሚስሽ ሥር ጭንሽን ከፈት አርገሽ
እንደ ማንም ነበር አንቺም የምታጨሺ? . . .
እንዲህ ነው ነጻነት እውነትም ታድለሽ!
እዚህ ሐገር እንደሁ
አጫጫሱ አያውቁ . . . ጭን መከፈት አይችሉ
ያ'ልቦ ከምር ብቻ . . . ፓሪስን ያልሆኑ
ኢትዮጲያን ያልሆኑ
የማይሰለጥኑ
አንቺን የሚመስሉ . . . እንዳንቺ የሆኑ
ኢጭ!!!

29-02-2004

ግማሽ - ባዶ ሙሉ

ገጽ ___
ገጽ 31
ገጽ 39 . . .የሚባሉት ገጥሞች
ያስጠላሉ ብለሽ ላገር ለመንደሩ ታወሪያለሽ አሉ
ሥራ የሚያስፈቱሽ
ዕድሜሽን የበሉ ስንቱ ሴቶች ሁሉ
አንቺ ፊት እውነትም ያስጠላል እያሉ ያበረታታሉ
ቡና ማኪያቶ እንዳልጠጡ ሁሉ
ወሬ እያጋፈሩ እንዳልዋሉ ሁሉ
ሐሜትሽን ሊነግሩኝ _ ወደ'ኔ ደወሉ
አቃጣሪ ሁሉ . . .
በነገራችን ላይ . . .
ገጽ 31
ገጽ 39 የሚባሉት ገጥሞች ማን ያንቺ አረገው
ማንስ ላንቺ ጻፈው?
ይቅርታ አድርጊልኝ . . . ዕድሜሽ ሰላሳ አልፏል!
ላ'ርባ አንድ ፈሪ ያንቺ 'ዕድሜ ይሆናል?
ቢሆንም ባይሆንም . . . መታሰቢያ እንዲሆን
የግጥም ርዕስ . . . የገጽ ቁጥርም ለአንቺ ብዙ ነው
ላንቺ የሚገባሽ
ከዚህ ገጽ በታች 'ምትመለከቺው . . . ባዶው ሉክ ብቻ ነው።

ቀዝቃዛ እቦል ሴት

አንድ የሻማ ብርሃን ነፋስ የሚገርፋት
ወይ ድምቀት አትሰጥ ወይ አየር አይገድላት
ያንቺን ሕይወት አይነት
ጭል ጭል እያለች
በራሁ ጠፋሁ ብላ ልቤን እያባባች
መቅረዝ ላይ ተቀምጣ ትወዛወዛለች።

ከጠረጴዛው ላይ
የጀበና ቡና በስኒ ተቀምጧል
ገጣሚው
ግጥም ሲጽፍልሽ ቃላት ይቀምራል
ፊደል ይሰርዛል።

እኩለ ሌሊት ነው . . .
የሙዚቃ ዜማ ከቴፑ ይሰማል።
የጌታቸው ካሳ . . .
'ዕንቅልፍ እንቢ አለኝ ሻማ እያበራሁኝ
ዛሬ ስሌዳ ላይ ዐምናን እየጻፍኩኝ
በትዝታ ዜማ ዕድሜዬ ላይጠና
በአምባሰል ቅኝት ቃላቴ ሣይቀና
በካቻምናው ሜዳ ያፈቀርኩት ዘጠኝ
ትዝታ ምኔ ነው . . .
ሠላሣ ሳይሞላኝ።
ይላል።
ሙዚቃ እየሰማሁ
ነፋስ የሚገርፋት ሻማዋን እየኋት
ዕድሜዬን ተውኩና . . . ዕድሜሽን አሰብኩት
ወንድነቴን ትቼ
ያንቺን ውብ ሴትነት ሰው ሆኜ ልብ አልኩት
መቅረዝ ላይ ያለችው
ፀዓዳ ሻማዋ
ከወደ አናቷ ወደጎን አልቃለች
የለኮሰኳት ከብሪት
ልጅነቷ ጠቀሮ እግሬ ስር ወድቃለች

ይቅርታ አድርጊልኝ
በሰው መሆን ልቤ ሲትነትሽ ገባኝ
ሻማ በሌለበት . . .
የ'ንድ ሻማ መብራት ከንቱ እንደሆን ታየኝ
አሁን
የሙዚቃው ዜማ ከቴፑ ስር ጠፍቷል
ላንቺ ማስታወሻ
ለመጻፍ የምሻው
የግጥሜ ሃሳብ ከ'ይምሮዬ ተኗል።
እጅግ የምወደው የጀበናው ቡናም ሥኒው ሥር ቀዝቅዟል
በጣም ያሳዝናል . . .
ዕድሜ እንዴት ይነዳል
ጊዜ እንዴት ይሄዳል።
-

ይህ ሁሉ ቢሆንም
በጆሮ ለመስማት እጅግ የሚከብደው
ወደ 'ውነት ለመቅረብ ምስሶ የሆነው
ይሄ ግጥም ግና ማስታወሻነቱ ለአንቺ ብቻ ነው።
በነገራችን ላይ ከጌታቸው ካሣ
'በካቻምናው ሜዳ ያፈቀርኩት ዘጠኝ
ትዝታ ምኔ ነው ሠላሣ ሣይሞላኝ
ስለሚለው መስመር
እውነቱን ብነግርሽ
በጣም ነው ሚገርምሽ . . .
አንድ . . .
እኔ ዘጠኝ ሴቶች አፍቅሬ አላውቅም
ሁለት . . .
ያን ዐይነት ትዝታ የዛን ዓይነት ግጥምም
በጌታቸው ዘፈን ተሰምቶ አያውቅም
ለምነው ካልሽ ግን
ያልኩትን ልንገርሽ
አንድ የሻማ መብራት ፀሐይ የሚገርፋት
ወይ መብራት አትሰጥ ወይ አየር አይገድላት
ያንቺን ሕይወት በየንት
ያንቺን ሕይወት መስላ ጭል ጭል እያለች
በራሁ ጠፋሁ ብላ ልቤን እያባባች

መቅረዝ ላይ ተቀምጣ ትወዛወዛለች . . .
ገጣሚው
ወንበር ተደግፎ
ገጥም ሊጽፍልሽ ቃላት ይቀምራል
የጀበናው ቡና
ከጠረጴዛው ላይ በሥኒ ተቀምጧል
የሚገርም ነገር
የሚያሳዝን ነገር
ይሄ ምርጥ ቡና አቦል እንዳልነበር
ትኩስ እንዳልነበር
ምላሴ ሳይነካው
በኔው ስር ቀዝቅዟል ከንፈር ሳይዳስሰው
ወይ አለመታደል . . .

## ገጽ አርባ በገሃድ

ውስኪ ቤት ቀረና
በየወንዱ እልጋ እንቦላ መጋፈፍ ትዝታ ሆነና
ከሰንት ዓመት ኋላ
አሁን በቀደም ለት በርሽ ላይ አየሁሽ
አየሁሽ
አየሁሽ
ሰማያዊ ቀለም ውስጥ ልብስ እ'ርገሻል
የተባበ ባላ-መሳይ ቅርጽ ሠርቶ የውስጥ ሱሪሽም ከውስጥሽ ይታያል።
እንዴት አምሮብሻል
ግን . . .
በጣሙን ገረመኝ . . . ደነቀኝ ገረመኝ
እንዲህ ዐይነት አልባስ አሁን በዚህ ሰዓት ምን
ያደርጋል አልኩኝ? . . .
በርሽ ላይ ቢሆንም መንገድ ነው የቆምሽው
ባልሽ ቤት ባይኖርም
ገላሽ ግልጽ ነበር ላላፊው ላገዳሚው
ማንም ባያቅፍሽም
ማንም ባይስምሽም
ገላና በርሽ ግን ተከፍቶ ነበረ ምንም ሆይ ለማንም።

29-02-2004

## የሰባ ዓመት ንጉሥ

ከሰባ ዓመት ኋላ
በየቱም የ'ድሜ ሥፍር አሁን ቆመው ያሉ
በተፈጥሮ ግዳጅ ሁሉም ይጓዛሉ
አንድ . . . አንድ . . . እያሉ።
ጥቂት መንገደኞች . . .
የእግር የ'ጃችውን አሻራ አስቀምጠው በ'ርግጥ ይሄዳሉ
ብዙ ተጓዦች ግን . . .
'ምንም' አይባሉም ካለ መፈጠር ጋር እኩል ይሆናሉ።
ሰው እንዳልነበሩ
እንዳልተፈጠሩ።

29-02-2004

ላርባ አንድ ፊራ ፺

አታውቂኝ አላውቅሽ
ገጽ 31
ገጽ 39
ገጽ ___ የሚለው ያን መሳይ ውብ ግጥም እንዴት ያስጠላኛል
በርግጥ አላውቅሽም
አንቺ ግን አርባ 'መት ጠጋ ማለትሽን መገመት ይቻላል
ምክንያት
ምክንያት . . . ተናደሻል
የገጣሚው እውነት ልብሽ ተሰምቶታል
ባክሽ አታስመስይ
በየውስኪ ቤቱ እድሜሽን ጨርሰሽ
በየመንገዱ አልጋ ውበትሽን በልተሽ . . .
እንደኖርሽ
መገመት ያቅታል
እንደው ባልገምትስ
አሁን በኛ ሐገር . . . እንደዚህ የኖረ አንድ ሰው ይጠፋል?
እና! . . .
እና ማለት መልካም
አታውቂኝ አላውቅሽ
እውነቱን ሥነግርሽ የዚህ ግጥም ሃሣብ አንቺን አይወክልም
አጋጣሚ 'ንጂ የታሰበ አይደለም
እናም የማላውቅሽ
በየውስኪ ቤቱ እድሜሽን የጨረስሽ
በየወንዱ አልጋ ውበትሽን የበላሽ
አንቺ የማላውቅሽ
ባክሽ ደውይልኝ
ባክሽ
ባክሽ
ባክሽ
ደውይልኝና ከዚህ ግጥም ግርጌ ሥምሽ ይጻፍልሽ።

29-02-2004

## አንድም ሦስትም

እንድ ተራ መጽሃፍ
እጆቿ ላይ ይዛ ብዙ ዘመን ሆናት
መጻፉ ተነቧል
የሆነ ቦታ ላይ ገጹ ተገንጥሏል
የተገነጠለ የመጽሐፉን ሐሳብ ባሳቧ እየሞላች
በ'ሊሆን ይችላል እየተማመነች
ተራውን መጽሃፍ ድሮ እንብባዋለች
ድሮ
ድሮ . . . ድሮ
አስራ ሁለተኛ ክፍል ልክ እንደጨረሰች
እንገዲህ
እስከ ዛሬ ድረስ በጇ ላይ 'ሚገኘው
ይሄ መጽሃፍ ነው!
የመጽሃፉም ርዕስ . . .
'ሚቆጨኝ ዘመናት
ተራራን የናዱ
አስደንጋጭ አናብስት
ይሕንን የናቀ
ያ-ትውልድ የሚባል ልዩ መጠሪያ አለው
በነገራችን ላይ የሚገርመው ነገር
ይሄ ከንቱ መጽሃፍ የራሷ ድርሰት ነው
ወይም . . . ራሷን ነው!

29-02-2004

በድጋሚ ለ______

ፈረንሳይ እያለሁ
የዛን አይነት ግጥም
ያጻጻፍም ዘዴ አይቻለሁ ብለሽ
ለነማን ነበረ
ማንኪራ ተቀምጠሽ
ሥታወሪ የዋልሽ
ለነማን ነበረ
እዎ
ምድረ ከንቱ ሁላ
በየኋላ ኪሱ ግጥሙን ቦርሳ አድርጎ 'ሚንከራተት ሁሉ
እንዲህ አይነት ግጥም
ከአንድ ኢትዮጵያዊ ሊጻፍ የሚቻለው
ካንድ ምርጥ ፈረንጅ ሲኮርጅ ብቻ ነው
እያሉ ይላሉ ምድረ ከንቱ ሁላ።
ያወራሻቸውን ለኔ ያወራሉ
ታዲያ እንዲህ ያሉ ጻፊ ይባላሉ
ያላነበቡትን የሚያወሩ ሁሉ
ጆሮ ጠገብ ሁሉ
የሚገርምሽ ነገር አንቺ በኔ ንደት
አንቺ በኔ ፍቅር
የሌለውን ፈጥረሽ እንደምታጣጥይ አልነገርኳቸውም
ከነገርኩኝ'ማ
ሌላ ጊዜ መጥተው እኔን ያማሽኝን ለኔ አያወሩም
ምክንያቱም ፍቅር አለ
ግና አደራሽን
በፍቅሬ ተናደሽ ግጥሜን ስታሚው
ፈረንሳይ ምናምን ማለትሽን ተይው
ምክንያቱም . . .
እዚህ በኛ ሐገር ፈረንጅ አገር ሄዶ የተመለሰ ሰው
እዛ ፈረንጅ ሐገር ቦዘኔ 'ንኳ ቢሆን
ምሁር ተደርጎ ነው
የሚተረጎመው።

29-02-2004

ላይንና ለጆርሽ ሁለት ሥጦታዎች

አራዳ ፒያሳ
ትሪያኖን ሬስቶራንት ከበረንዳው ላይ ነኝ
ወጭና ወራጁን
ሒያጅና መጭውን
የሚሳፈረውን ደግሞም ሚወርደውን እየገመገምኩኝ
ከጠረጴዛው ላይ
የቀዳም ጋዜጣ የማኪያቶ ሥኒ እጄ ላይ መጽሐፍ አለንጋና ምስር
ተብሎ የሚጠራ
ግራ ጣቴ መሃል ሮዝማን ሲጋራ።
ጎኔ ከሚገኘው
ከሙዚቃ ቤቱ ከዳላስ መካከል
ሙዚቃ ይፈሳል
l'ove remember that we forget የሚል
ሙዚቃውን ሰምቶ ቆም የሚል ሰው የለም
ሁሉም ሰው ተጓዥ ነው ከየትም ተነስቶ ሊደርስ ወደ ምንም
እጄ ላይ ያለውን መጽሐፍ ገለጥኩት የገለጥኩት ቦታ ያ ሐመልማል ይላል
ያን ታሪክ አንብባም
አንዲት ሴት የለችም ወደደኩት የምትል
ያን ታሪክ አንብቦም
አንድ ወንድ አይገኝም እንኪ አንብቢው ብሎ ለሚሰቱ 'ሚያቀብል
ሙዚቃውን ሰምቶ ዝግ የሚል ሰው የለም መርሳት ይፈልጋል ራሱን ዛሬንም
መጽሐፋን አንብቦ ቆም የሚል ሰው የለም
ሁሉም ሰው ተጓዥ ነው ከየትም ተነስቶ ሊደርስ ወደ ምንም
ጆርጅ ቤንሰን ሙዚቃውን ጨርሷል
አሁንም ደግሞ
የትሬሲ ቻፕማን ደምቆ ይሰማኛል

Sorry is all that you can say
Years gone by and still
Words do not come easily
Words like sorry, forgive me, I love you
but but
You can say it!
You have to say it I love you I love you

እያለ
የትሬሲ ድምጿ
መሐል ፒያሳ ላይ አየር ላይ ይገኛል
እጄ ላይ 'ሚገኘው
ክቡር ሰው የጻፈው ክቡር መጽሐፍ ደግሞ
እንዲህ ሲል ጅረቱን ባህር ጥግ ያስተኛል
"ጣውላ ከረገዘ ሰውነቴ
ዕንባ መውጣት ጀመረ። እናም ማልቀስ ጀመርኩ"
ያንን እየሰማሁ ይህንን ቃል እነበብኩ
አንቺን እያስታወስኩ ይህንን እኔ ጻፍኩ።

02-01-2005

ምንምን ዳግመኛ

አደራ ለቀዐዬን በልቶታል አትበይ
ከንቱነት መሞቱን
ጎዳና ሰምቼ ቤትሽ መጥቻለሁ
ቢሆንም
ከንቱነት አካሉ ካፈር ቢቀበርም
ከንቱነት መንፈሱ
ከቤት እንዳልጠፋ ይህን ግን አውቃለሁ
ደግሞም እይቻለሁ
መቼ?
ለቅሶሽ የመጣሁ ቀን ካርባ ቀን በኋላ
ግርግሩ ሲቆም
መበተን ሲጀምር አድርተኛው ሁላ
ምን?
መቼም አመል ከፋ ነገር ምንም ይሁን ምንም
አንቺን ፈጥኖ እንዲለቅ በ'ግዜር አልተጻፈም
እናም!
ምን በይኝ ግድ የለም
እንዳላየም ሆንሽ መቼ በይ ግድ የለም
እንግዲያው
እሀ ብለሽ ስሚኝ
መቼን እና ምንን ላስታውስሽ አድምጪኝ
ያኔ
ትዝ ይልሽ እንደሆን
አንቺን ለማጽናናት ለቅሶሽን ለመድረስ ቤትሽን ስሳለም
ያ . . .
የትም የሚባለው
የከንቱ ጓደኛ ያ-ከንቱ ያ-ደፋር
ፊቱን ላብ አጥምቆት
ከመኝታ ቤትሽ ጋደም ብሎ ነበር።
ወይም ከተረሳሽ
አንቺ . . .
ወደ ጓዳ ገብተሽ
ለመሥራት ፈልገሽ ቁርስ ቢጤ ነገር
የኔን ድምጽ ሰምተሽ ድንገት ከሳሎን በር

የሆነ ብርጭቆ ከጅሽ አፈትልኮ ተሰባብሮ ነበር።
አሁንስ ትገዢ አለሽ? . . .

29 - 02 - 2004

ገጽ 39 እንዳዲስ ዳግመኛ

ናፈቅሽኝ
ናፈቅሽኝ
ናፍቆት ስለበዛ ለዚህ ነው ምጽፈው
ያየሁሽ እንደሆን
የባልሽ ሙት ዓመት የዛ ’ለት ብቻ ነው።
እጄ ላይ የቀረው የናፍቆት መወጫ
ይህ ግጥም ብቻ ነው
የዚህ ግጥም ’ርስ መናፈቅ ብቻ ነው
ላንቺ
በድጋሚ
እሺ ይህን ግጥም በቃ ላንቺ ልሰጥሽ
ምክንያቱም
በዚህ ተራ ግጥም ድንገት ተበሳጭተሽ
በድንገት ተናደሽ
እኔን ለመሳደብ ወይንም ለመምከር
እንዲህ ዓይነት ግጥም ካንተ አልጠብቅም ብለሽ ለመናገር
ከበራፌ መጥተሽ
ደጃፌ ላይ ቆመሽ ድንገት እንኳ ባይሽ
ይህን ተራ ግጥም ምክንያት እንዲሆነኝ ተቀበይኝ ባክሽ።
ድንገት
ድንገት
ድንገት

29-02-2004

ናፍቆት

የባልሽ ሙት ዓመት ዛሬ ይከበራል
ዛሬ ይታሰባል።
ታድያ ምን ያደርጋል?
እርሱን ያገባሽ 'ለት አንቺ መሞትሽን የትኛው ሰው ያውቃል?
-
የባልሽ ሙት ዓመት ዛሬ ይከበራል
ዛሬ ይታሰባል።
ታድያ ምን ያደርጋል?
ተፈጥሮ በድንገት አንቺን የጠራች 'ለት ማን ይገንዘሻል?
-
የባልሽ ሙት ዓመት ዛሬ ይከበራል
ዛሬ ይታሰባል።
እናም . . .
እኔን ደስ ብሎኛል
ይህን ከሚመስል አጋጣሚ በቀር ዐይኔ አንቺን ለማየት መች ተፈቅዶለታል

29-02-2004

ገፆች

እንዳንዶች
ይቅርታ አድርጊልኝ
እንዳንዶች ነው'ንጂ ማንም አላልኩሽም
ደግሞም
የማንም ሰው ምክር በፍጹም አልሰማም
ይቅርታ
ይቅርታ . . . ይቅርታ
አየሽው ሥህተቴን
አየሽው በደሌን
ይህንን መሳይ ገጽ በከንቱ ማጥፋቴን
ማበላሸቴን
አየሽው በደሌን
ግን ምን ማለቴ ነው
ምንስ ማድረጌ ነው
ማንም በተፈጥሮው ማንም ሆኖ ሳለ
ማንም ነኝ እያለ
የኔን ግን ተመልከች
ስህተቴን ጥፋቴን
የእኔን
የማንም ሰው ብዬ ማንምን መጥራቴን
ተመልከችው ግፌን
ደግሞም የሚገርምሽ
ሥላንዳንዶች ልጽፍ ልነግርሽ አስቤ
ይቅርታ ማለቴን
በጣም መፀፀቴን . . . ብቻ ተመልከችው ሁሉም እንደሆነ ከንጀቴ
ከልቤ
ከልቤ
ማንምን ሰው ብዬ ሉኮችን ማርጠቤ

29-02-2004

ይህ ርዕስ አይደለም

ይድረስ
ለገጽ 31
ለገጽ 39
እንዲሁም ለገጽ ____
መቼም ሥጦታዬን ሁሉን ንቃሸዋል
እንዴት ይመስልሻል?
ማለት? . . . ምን መሰለሽ
ድንገት አዲስ አሳብ ለኔ መጥቶልኛል
ሃሳቡን ሳስበው ለኔ አሪፍ መስሎኛል
ሃሳቡ ምንድ ነው?
አሪፍ ጥያቄ ነው
(ሃሳቤን ልንገርሽ)
ያው እንደምታውቂው
የጣ'ፈንታ ነገር ከኔ ለይቶሻል
ገንዘብን አፍቅሮ
አፍቃሪን መከዳትም መቼም የማትፍቂው ታሪክ ሆኖብሻል
ግን ስለምወድሽ
በዚህ መጽሃፍ ላይ
አሪፍ መታሰቢያ ላንቺ ተሰጥቶሻል
ስላንቺ ታይቶኛል
እርሱም . . .
ከዚህ መጽሃፍ ጀርባ
የዚህ መ'ፃፍ ዋጋ የሚለው ቦታ ላይ ያንቺ ስም ቢቀመጥ
እንዴት ይመስልሻል

30-02-2004

የጣ'ሊን ፈገግታ ገጣሚ ሲያለቅሰው

በዚህ ቃል እምናለሁ
ታላቅ እውነት አለው
የሠዓሊውን ፈገግታ ገጣምያን ያለቅሱታል
ግን . . .
የገጣሚው ዕንባ
ከብዙሃን ፊት ላይ ሳቆችን ይወልዳል።
. . .
በዚህም እምናለሁ
ባይናቼም ፊት ለፊት ዞትር እየዋለሁ
ከ'ናቶች ታለቅ ምጥ ልጆች ይገኛሉ
የጸደይ አበቦች
ከረምት ጀርባ ላይ ታዝለው ይመጣሉ
ደግሞም
ከብዙ ጭንቀቶች
ከ'ንቅልፍ አልባ ሌቶች
እጅግ ምርጥ ሃሳቦች ተወልደው ያድጋሉ
-
(ይህንን ስነግረው)
ቃሎቹ ጉም ሆነው ዓይኖቹ ወንዝ ሆኑ
ወደ ራሱ ገባ ሣቆች ደመኑ።
ነገሩ እንዲህ ነው
ሠዓሊው ወዳጄ
ምርጥ ሥዕሉ ፊት ፈገግ ብሎ እያየኝ
አልሸጠውም ብዬ ያስቀረሁት ብሎኝ
የራስ ምስል የሚል ሥዕሉን አሳየኝ
ሥዕሉ?
ዐይን የፈጠጠ
ዐፅም የገጠጠ
አጥንት ያፈጠጠ
ደረት የተበሳ ሠማይ የተሰፋ
ግራጫ ቀለማት ከሸራው ጀርባ ላይ
ሠማይ
ጥቁር ሠማይ
ከአናቱ በላይ። . . .

ከከንፈሩ መሐል ሲጋራ ያለቀ
ከጎኑ ደብዳቤ ለሴት የረቀቀ
ከ . . . እኔ . . .
ለ . . . እኔ . . .
ዝብርቅርቅ ጽሁፎች
ፍቅር
ፍቅር
ፍቅር
ናፍቆት ፍቅር ናፍቆት
ፀፀት
ፀፀት ፀፀት
እኔ ነኝ የጻፍኩት ይድረሰሽ ለእኔ
እንዴት ላንቺ ልበል እንቺኮ ነሽ እኔ
ወይኔ
ወይኔ ወይኔ
-
በጣም ያማል አልኩት
አልሸጠውም አለኝ
ዐይኖቹ ረጠቡ ልቤን እንባ ሞላኝ
ትንሽ ግራ ገባኝ
-
ያብራራልኝ ጀመር
-
'የሚገርምህ ነገር
ይሄን ታላቅ ስዕል ደጁ ድረስ መጥቶ
ልግዛህ የሚለኝ ሰው
ናፍቆትና ፍቅሬን የነጠቀኝ ሰው ነው'
የሚያሳዝን ነገር
ይህ ከንቱ ሰውዬ
ሥዕል የሳሎን ጌጥ
የቤት ማሳመሪያ የሚሆን መስሎታል
መስመር ስር ዕድሌ
ከቀለም ጋር ደሜ መኖሩን ዘንግቷል
በደሉን ረስቷል
ተንኮሉን በብሩ
ሊጋርደው ይሻል

ዳግመኛ ሥዕሉን ቀና ብዬ አየሁት
አጥንት የፈጠጠ
አጽም የገጠጠ
ዐይን ያፈጠጠ
ደረት የተበሳ ሰማይ የተሰፋ
ሰማይ
ጥቁር ሰማይ
ከእናቱ በላይ

24-02-2004

መግቢያ

ገጽ 31 እንደምን ከርመሻል
ገጽ 39 እንዴት ሰንብተሻል
ላርባ አንድ ፈሪ ኑሮ እንዴት ይዞሻል
ሴት መሆን ይጨንቃል
እኔ ምልሽ ማነሽ
ክርስትና ስሜ ማነሽ ነው ያልሽ እንስት
ማታውቂኝ ማላቅሽ ብቻ ግን ያየሁሽ አንድ የሆነ ቀን ከሆነ አንድ ቤት
የሆነ ገጽ ላይ የዘልዓለምነት መጠሪያ እንዲሆንሽ
ሥምሽን ስለማላውቅ
ደውይ ብዬ ነበር እንድጽፍ ስምሽን
ከግጥሜ ግርጌ ስር
(በቃ ተይው ይቅር)
ግርጌው ይቅርና
ግርጌው ይቅርና
ግርጌ ሥር ላንቺ ስም አይመጥንምና
በቃ በዚህ መጽሃፍ
መግቢያ የሚለው ቃል ላንቺ መታሰቢያ በራስሽ ስም ይጽና
ምክንያቱም
የትኛውም መጽሃፍ
በማንም ሰው ቢጻፍ መግቢያ አያጣምና።

29-02-2004

# ጊዜ

ግቢዬ ያለችው
ጽጌሬዳ አበባ
መሐል ልቧ መሐል መድረቅ ጀምራለች
ውሃ ግን አላጣች
ማለዳና ምሽት ውሃ ትጠጣለች
ዘመን ከደረሰ
ውሃ አቅም የለውም ተፈጥሮ በራሷ እጇን ትሰጣለች
ያቺ ውብ አበባ
ከወደ አንገቷ ዘንበል ብላለች
ከወደ ልቧ ላይ ደረቅ ብላለች
ማንን ትመስላለች?
አየሁሽ በቀደም ትዝ አለኝ የጥንቱ
ፅጌሬዳ እያለሽ
ምርጥ ቪላ ያለው
ምርጥ ገንዘብ ያለው የማግባት ምኞትሽ አሁን ሆኖ ከንቱ
ልክ እንዳበባዋ
ያቺ ፅጌሬዳ
መሐል ልቧ መሃል መድረቅ ጀምራለች
ውሃ ግን አላጣች
ማለዳና ምሽት ውሃ ትጠጣለች
ታዲያ ምን ዋጋ አለው
ዘመን ሲበረታ ውሃ አቅም የለውም ተፈጥሮ በራሷ እጅ ትሰጣለች።
ጊዜ ፈቀቅ ሲል!

30-02-2004

ብዙ ገጾች

የሆነ ገጽ ላይ
አንዳንዶች ሚሉትን
ካንቺ የሠሙትን
የሆነ ገጽ ላይ ጽፌ እንደማሳይሽ ነግሬሽ ነበረ
ነበረ . . .
ምን አሉ መሰለሽ . . .
የርሱ ግጥም ማለት የቃላት ጨዋታ
የግሉ እሪታ
የራስ ዓለም ዋይታ እንጂ ግጥም አይደለም
ትላለች እያሉ . . .
የሚሉትን ሁሉ
ልነግርሽ ብፈቅድም
እኔ እንቺን ሳወራ
ላሜተኛ ሁላ . . . ክብር አይሁን ብዬ ተውኩኝ ምርጥ ግጥም
በነገራችን ላይ
እዚህ መጽሐፍ መሐል . . . ጥቂት ተራ ግጥሞች መከተት ያስፈለገው
ምክንያቱ ምንም ነው
እርሱም
ብዙ ገጾች ያሉት መጻፍ እንዲኖረኝ አስቤ ብቻ ነው።
ይሄ ግን ይሻላል . . .
ይሄ ምንም ሳይሆን አንድ ነገር አለው።

29-02-2004

## እሱ ባንቺ ቦታ

ፍርሃቴ ባሰ
ሥጋቴ ነገሰ
ክረምት የጀመረ
ደመና የዞረ . . . ይመስላል
እንዴት ያሳዝናል?
. . .
የወጣትነቷን ጊዜዋን የናቀች
ስንቱን ያፈቀረች
ምንም ፍቅረኛዬን
የልጅነቴን . . .
ክረምቱና ብርዱ እንዴት አድርጓታል?
(እያልኩ እስባለሁ)
የኔን ነገር ተይው
እስከዛሬ ድረስ በምንም ታስሬ
አንድ አንቺን አፍቅሬ
ውበቷ ያለቀ
አበባዋ የደረቀ
የረጀች
ያፈጀች
ከያኔ ተጋብታ ካሁን የተፋታች
አንድ እርሷን ወድጄ
እኔ 'ምን' . . . 'ምንምን'
ምንምን አፍቅሬ 'ምን' መሆን አለፈ
ፀደይ ወጣትነት ደረቀ ረገፈ
ይባስ ብሎ ደግሞ ክረምቱ ጀመረ
ደመናውም ዞረ
ፍርሃቴ ባሰ . . . ሥጋቴ ነገሰ
እንዴት ያሳዝናል?
ለካስ ካንቺ ጋራ የኔም ክረምት ሆኗል።

30-02-2004

ምልከት

ሲጋራ እያጨስኩኝ ቡና እየጠጣሁ ነው . . .
ካፌው 'ምን እንዲባል ሥሙን ግን አላውቅም
ደግሞም አንዳንድ ቤት 'ምንም' ስም የለውም።
ማኪያቶ እየሸጠ ቡና እየጨመቀ . . . ስም እንደሌለው ቤት
ይመስላል ያንቺ ሕይወት።
ቡናውን ልጨርስ እንድ ጉንጭ ይቀራል
ሲጋራውን ልጥል አንድ 'ፓፍ' ይበቃል . . .
ምንም ወዳጄ ሆይ ከነዚህ ከሁለቱ የትኛው ቢቀድም አንቺን ደስ ይልሻል?
እንባቢ ሆይ . . .
ምን ማለት ነው ብለህ ይሄ ትንሽ ግጥም በጣም ከገረመህ
ወይንም ካስጠላህ
መልሱን እኔ ልስጥህ
በቃ ላንድ ጽሁፍ ምንም መልካም ሃሳብ ቁም ነገር ከሌለው
ባፍሪካ ላይ ያሉ የብዙ ሴት ልጆች ፎቶ ግራፍ ያ-ነው።
እልያም በኢትዮጵያ
የሚመጣው ትውልድ ምልከቱ ያ ነው።

30-02-2004

ሕልምሽ ትዝ ሲለኝ

የሲጋራ ወረቀት
የብልጭልጩ ጀርባ ላይ
ዛሬ
አንድ ጽሑፍ አነበብኩኝ
ጽሑፉ ደስ አለኝ
ደግሞም አስገረመኝ።

. . .

ፍቅር ማለት ይላል
ጠዋት በማለዳ ስትነቃ ከእንቅልፍህ
ያላንዳች ጨዋታ ላንድ ብቻህ ሆነህ
ትንሽ ፈገግ ካልህ
ያኔ ፍቅር ሥር ነህ።
ይላል

. . .

ፍቅር
ፍቅረኛሞች
አብረው ሲሆኑ አይደለም
አብሮ መሆንን ሲያስቡ ነው
የፍቅር ትርጉሙ ፍጹም የሚሆነው
ደግሞም
ፍቅረኛሞች
ፍቅርን ሲሰሩት አይደለም
ለመስራት ሲጀምሩ
ነው። የፍቅር ትርጉሙ ፍቅር ቀም ነገሩ
ፍፃሜው አይደለም እንጂ ነው ጅምሩ
ይልና . . .
መጨረሻ አካባቢ
ፊርማና ስም ካለበት ቦታ ላይ ገጹ ተቦጭቋል
ይላል።
ያልተቦጨቀን ገፅ
ተቦጭቋል ቢሉ የሰው ፅሁፍ መስሎኝ
ለካስ ራሴው ነኝ
ትንቢት ይሁን ብዬ
ሕልምሽ ትዝ ሲለኝ መንገድ የጣፍኩትኝ።

ሌላ ______

ሻይ ቡና ለማለት
ከተማ ስትወጪ
'ሁሉን አይቻለሁ' እያልሽ በጉራ ታወርያለሽ አሉ
ሁሉንም ወንድ አይቶ
ሁሉን ሕይወት ማለት እንኳ እንቺ ቀርቶ ሴቶቹ በሙሉ
በኢትዮጵያ ያሉ
እንደዚያ ይላሉ።
'ታድያ ምን ይገርማል? . . .
ይህ እንቺን ካኮራሽ
መንገድ የምትቆመው ሌላ ______ ምን ትበል።

30-02-2004

አዛኝ ቅቤ አንጓች

ፓሪስ የቀረውን
የድሮ ትዝታ ለቤት ሰራተኛሽ ታወርያለሽ አሉ
ማኪያቶ እየጠጡ ከኔ ጋር ያጣሉሽ ጓደኞችሽ ሁሉ
ዛሬ? ዛሬ ወዴት አሉ?
-
መልካም ልጅ ነበረ
ብለሽ ለዘበኛሽ አንዳንዴ ስለ'ኔ ታወሪያለሽ አሉ
ባልሽ ላይ ደርቦ ካንቺ ጋር የተኛው
የመቼም ባለቤት እነ የትም ዛሬ ከወዴት ነው ያሉ?
-
እንዴት አንዲት ሴት ልጅ
እግዜር ይነሳኛል ብለሽ እግዛቤርን ታሚዋለሽ አሉ
ታማርያለሽ አሉ
ጸደይ ሳትቀዘቅዝ አብረን ፀሐይ እንሙቅ እንዳላልኩሽ ሁሉ
-
ዛሬ የኔ ሕይወት
በድንጋይ ቤት ድንጋይ ከመሆን ከፍ አይልም
እያልሽ ለጓደኞችሽ ታወርያለሽ አሉ
ከቤትሽ ሲወጡ
ደጃፍሽ ላይ ቆመው ያልሽውን በሞላ ለኔ ያወራሉ
ምክንያቱም
እስከ ዛሬ ድረስ እኔ አንቺን መውደዴን አውቃለሁ ያውቃሉ
ግን
ያልሽውን በሙሉ ቅስምሽ መሰበሩን ለኔ ግን ሲነግሩ
አዝነው እንዳይመስልሽ ነው ቅስሜን ሊሰብሩ።

30-02-2004

## አንግር !!

ምንም ወዳጁ ሆይ
ትንሿን እህትሽን ማከሰኞ በድንገት መንገድ ላይ አየኋት
ውበት ደም ግባቷ የድሮው አንቺ ናት።
ደግሞም መቼ ለታ
የመቼም ሴት ልጅን ከነንድ ጎረምሳ ጋር ፊልም ቤት አየኋት
ድሮስ <u>የማን</u> ልጅ ናት?
ግና ሥጠረጥር
እህትሽ አንቺ ቤት መምጣት ያቆመችው
በራስሽ ምክንያት በራስሽ ሰበብ ነው
እርሱም
ልጅነት ውበትሽን እህትሽ ገላ ላይ እንዳታይ ብለሽ ነው።

30-02-2004

ዕለት

ቀን
በነሐሴ ዝናብ
በጭቃው መካከል
ቡሄ ነው እያለ አስቀዳሹ ሁሉ ቄጤማውን ይዟል.
ችቦውን ይገዛል።
ሕፃናት በርሽ ላይ መ'ተው ሲጨፍሩ ሆያ ሆዬ ሲሉ
ከሩቅ እየኋቸው
ውብ መንታ አይኖችሽ ዘለላ ዕንባዎች ከመሬት ሲጥሉ።

ምሽት
ሰዎች በየቤቱ
ባንድ ተሰባሰበው ችቦ ሲያቃጥሉ
እንቺን ግን ሰማሁሽ
ችቦ እጠገብ ሆነሽ ነፍስሽን ሲበርዳት
የሰራተኛሽን ትንሿን ሕፃን ልጅ ሂጂና ከጎዳ ጋቢ አምጪ ስትያት።

30-02-2004

ጥቂት ስለራሴ

ስላንቺ
ቃላቶች ስፈልግ ፈልጌም ስጸልይ
ስጸልይ
ስጸልይ
የእድሜዬ ጀምበር ገባች የኔ ፀሐይ።
ስላንቺ
ካንቺ በቀር ብዬ
እኔን ወድያ ጥዬ
አንቺን እንዲሰጠኝ እንዳ'ንቺን እንዳገኝ
ስጸልይ
ስጸልይ
ሄደች ወጣትነት አለፈችኝ ፀደይ!
ብዬ
ተከዝኩ
በሁለት መዳፎቼ ሁለት ጉንጬን ይዤ
ተቀምጬ ሳለ
መጣች ደግሞ 'አሁን' . . . አሁን . . . አሁን . . .አሁን
ከልቤ ያጠፋች የምንምን ፍቅር
አሁን ሄደች ስላት አሁን የምትኖር።
አሁን!

30-02-2004

ከብር ወይስ

የዚህ መጽሃፍ ዋጋ የሚለው ቦታ ላይ . . .
ያንቺ ስም ተጽፏል።
ያለማወቅ ነገር እንቺን የሰደብኩሽ የናኩሽ መሰሎኝል
በጣም ተሳስተሻል።
እንዴት

እንዴት ይመስልሻል
እሺ ይሁን እንበል
ግን
ላንቺ የተጻፈ ያንድ መጻፍ ዋጋ ምን ያህል ያወጣል?
ታድያ
እኔ ይሀን ግጥም ባንቺ ምክንያት ጽፌው . . . ገበያ ሳወጣው
ስድብ የሚሆነው
ንቀት የሚሆነው
የትኛው ነገር ነው?
የዚህ መጻፍ ዋጋ የሚለው ቦታ ላይ ስምሽን መጻፉ ነው?
ወይስ ሁለተኛው
ግለ ታሪክሽን ባ'ርባ ብር መጥፎ ባያደባባዩ መሸጥ መለወጥ ነው?
ንቀት የትኛው ነው?!

29-02-2004

## ስተተኛ እውነት

አሁን ካሁን ጋራ
በሚገርም ፍቅር ወድቄያለሁ ብዬሽ ነግሬሽ ነበረ
አሁን ከኔ ጋራ መኖሯ ነው'ንጂ
አሁን አሁን ስማኝ . . . አሁን ግን መጥፋቷ እውነት ሆኖ ቀረ
እናም
ምትመጣውን አሁን አሁን እየሳምኩኝ
የምትሄደውን ደህና ሁኝ እያልኩኝ
እየተናደድኩኝ
ጥንትም የቤት ጸባይ መምጣትና መሄድ አንድ ነው እያልኩኝ
የሄደች ምንምን
የመጣች አሁንን
የሁለቱንም ከንፈር በከንፈሬ ስሜ
በጊዜ ሳልሰራ ጊዜ ብቻ አፍቅሬ ውብ ወጣትነቴ ተበላች የኔ ዕድሜ።

30-02-2004

## ደባል ታቦት

ከንቺ ናፍቆት ጋራ . . .
በቀን ሦሥት ሮዝማን ዛሬም እጨሳለሁ
ግዮን ሐሳብ ወንዜን
በአልኮል ሸርሽሬ ወዳንቺ እፈሳለሁ
እስከመቼ ድረስ
ሲጋራ ጢስ አባይ
ጤግሮስ የውስኪ ማይ ሳመልክ እኖራለሁ።
ይሕ አይደል በደሌ
ይሕ አይደል ሐጢሀቴ
ማንም ሚባለማት መቅደስ ማበራቴ
ማንም
ማንም
ማንም?
ያ አይደል ሐጢአቴ
በዛው ቤተ-መቅደስ ላንቺው መሠዋቴ
ሁለተኛ ጽላት ደባል ማስገባቴ
ያ አይደል ሐጢአቴ።
ወዳጄ ሆይ ስሚ . . .
አዲስ መቅደስ ሊሥራ የቀደመው ይፍረስ
ደባል ታቦት ይውጣ አንድ ጽላት ይንገስ
ሲጋራ ጢስ አባይ
ጤግሮስ የውስኪ ማይ ፍጹም ከኔ አይፍሰስ
እንድ አምልኮ ያብቃኝ . . .
ከወፍራም ቡና ጋር ከነዚሀ ጋር ልኑር
ከቅኔ
ከሀደይ
ከሕይወት . . . ከፍቅር
ከኚሀ በላይ ደግሞ . . . ከንቺ ውብ ናፍቆት ጋር።

01-03-2003

መቼም

አንድ ቀን
ጥግ ላይ
አራተኛው ወንበር ከታክሲው ውስጥ ነኝ
አጠገቤ ሴት ልጅ
ወደጎን ምታየኝ የምታስተውለኝ
ልጅቷ . . .
ቀሚሷ አጭር ነው ጭኗ ይታየኛል
ገላዋ ነከቶኛል።
ከጡቶቿ መሐል ሽታዋ ይነሳል።
እኔ
አልቻልኩም
በፍጹም አልቻልኩም
የልቤ ፍጥነቱ ጨምሮ ነበረ
በታክሲው መስታወት
ወደ ውጭ እያየሁ አላይም ነበረ
ገላዋ 'ሳት ሊሆን ጀምሮት ነበረ
ገላዬ ሙቀቱ ጨምሮ ነበረ። ወደ ውጭ እያየን ወደ ውስጥ ነበርን።
ታክሲው ግን ፍጥነቱ? . . .
ፍጥነቱ።
ፍጥነቱ!
የሚገርምሽ ነገር . . .
የዚህች ቆንጆ ሴት
የገላዋ ቅላት እንደሚያዝያ ጀምበር
ጀምበር
ጀምበር
ጀምበር
ታዲያ ምን ያደርጋል . . . አሳዘኙ ነገር
የሴቲቱ ጊዜ
የመንገድ ዕድሜዋ በጣም አጭር ነበር
አጭር!
በጣም አጭር።
ወራጅ አለ አለች። . . . ድምጿ ራሱ ያምራል
ታዲያ ምን ያደርጋል?

02-03-2004

ተራ አስተያየቶች

ይሕን የኔን ግጥም
ይሕንን መጽሃፍ ያነበቡ ሁሉ
አንዳንዶች ይላሉ
-
ምን________?
የግጥሙ ሐሳብ
በግራም በቀኝም በፊትም በኋላም
ከጨለማ ሐሳብ ከከንቱነት በቀር ምንም አዲስ ሃሳብ በውስጡ የለውም
የለውም
የለውም
በፍጹም በፍጹም
ከከንቱነት በቀር
ምንም አዲስ ነገር . . . የለውም
ይላሉ
ግጥሜን
'ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር' . . . የሚል መጽሃፌን
-
ግን?
ግን?
እነሀ የኔ ግጥሞች በዚህ መጽሃፍ ያሉት
(በተራ ተርጓሚ)
ከንቱ የተባሉት ጽልመት የተባሉት
እያንዳንዱ ሃሳብ
በብዙ ገጣሚ ተጽፎ ብናየው
አንደኛውን አንዱ አንደኛውን ሌላው
ጽፈውት ብናየው
ምን ብለን ነበረ የምንተረጉመው።

02-03-2004

የራስ ምስል በራስ

እንዳንዴ ለቡና
ያለፈን ለማውራት
እንገናኝ ብዬሽ እንገናኝ የለ . . .?
የሚገርምሽ ነገር
በዛ ሁኔታ እንኳ አንቺ ላይ ያየሁት አንድ ትዝብት አለ
-
በቀጠርኩሽ ቁጥር . . .?
ሠሀት ማሳለፋ
አርፍደሽ መምጣቱ እጅግ በጣም በዝቷል
በዝቷል
በዝቷል
በዝቷል
ወሰን - መጠን አልፏል . . .
እኔ ግን ሲመስለኝ . . .?
ሕይወትሽ ከረምቷ ማስገምገም ጀምሯል
ምክንያት? . . .
የገዛ ፊትሽ ላይ ሰዓሊ መሆኑን በጣም ወደሸዋል።

02-03-2004

ስንብት

አሁን -
በጣም ከባድ ዝናብ መዝነቡን ጀምሯል
አየሩ ይከብዳል
ትንሽ በረድ ይላል።
በይ እንደልማድሽ
በርሽን ቆልፊሽ . . . ጋቢ ደረብ አርገሽ
መስኮትሽን ዘግተሽ ሣሎን ከሶፋው ላይ ትንሽ አረፍ በይ
ከዚያም ግድግዳው ላይ
የተሰቀለውን ፎቶሽን ልብ በይ
በዚህ ዕድሜሽ ነበር . . . ?
አፍቅሬሽ የነበር።
በዚህ ዕድሜሽ ነበር . . . ትተሽኝ የነበር
በዚህ ጊዜ ነበር . . .
ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር . . .
የሚል ውብ ግጥሜን ዕፈልሽ የነበር።
በዚህ ዕድሜሽ ነበር።
-
አሁን
አሁን ግና
እስከ አሁን ድረስ ከነገርኩሽ ይልቅ ያልነገርኩሽ ነገር
ልብ ያላልሽው ምስጢር
ጊዜ አስረድቶት
የግድግዳሽ ሰዓት መስራት እንዳቆመ እርሱን ብቻ ነበር።
ምንም ወዳጄ ሆይ . . . በይ እንግዲህ ቻዎ!!!
ቻዎ!

29-02-2004

ሁሉም ከንቱ ነበር

የፓሪስ ጎዳና
ያዲስ-አባ ቡና
ከንቱ
ከንቱ ነበር
ባሁን ተጀምሮ በነበር የሚቀር
ሁሉም ከንቱ ነበር
በሽቶ መታጠብ
ውስኪ ቤት መሰብሰብ
ያለ ጥበብ መጥበብ
እስመስሎ መኖር
ካንዱ ጋር ጠጥቶ ካንዱ ጋር መተኛት
ያለ ሕልም ሕይወት
እንደ ጀምበር ጠልቃ ቀዝቅዛ ልናያት ፀደይ ወጣትነት??? . . .
ሕልማችን መተኛት
ሕልማችን መጠጣት
ተሰብስቦ ማውራት ማውራት ማውራት ማውራት
እዎን በዚህ አገር
ሁሉም ከንቱ ነበር
ሽማግሌው ማውራት
ወጣቶቹ ማውራት
ነገስታቱ ማውራት
ማውራት ብቻ ጥበብ ሕይወት የሆነባት
እርሷ ኢትዮጵያ ናት።
ኢትዮጵያም ምንም ናት
ማንም የሸመናት
ወርድና ቁመቷን ሳይመዝን ሳይለካት።
እናም በዚች አገር
ብዙው ብዙው ነገር እጅግ ከንቱ ነበር
በቃ ሁሉም ነገር
ቀለለ ተበላሸ ሕልም ተኮላሸ
'ምንምነት' ሰፋ 'ምን' መሆን ቆሸሸ
ምንም ወዳጄ ሆይ
እኔ ካንቺ ፍቅር
በሽበት እድሜ እንኳ የተረፈኝ ነገር

ምንም

ምንም . . . ምንም
ምንም ብቻ ነበር።
ሁሉም ከንቱ ሆነ
በሽቶ መታጠብ
ውስኪ ቤት መሰብሰብ
ያለጥበብ መጥበብ
ከንዱ ጋር ጠጥቶ ከንዱ ጋር መተኛት
እንደ ጀምበር ጠልቃ ቀዝቅዛ ልናያት ፀደይ ወጣትነት
ያለፍቅር ሞትን
ገንዘብ ተሸከመን ገንዘብ ሕልም ነሳን
ወሬ ብቻ ቀረን
ማንም . . . ምንም . . . የትም . . .ሦሥቱን ብቻ ሆነን
እንዲያ እንዳልነበርን
እንደዚህ እንዳልነበርን
እንደ ምንም ብለን ወሬ ብቻ ቀረን
ወሬ
ወሬ
ወሬ
ሁሉም ከንቱ ነበር . . . ሌላ ዓለምማ ነበር ነው የሚባል
በኛ ሐገር ግና ሁሉም ከንቱ ሆነ
የእንቺ ትዝታ የፓሪስ ጎዳና ባልኮል በሲጋራ እንደተጻፈነ
ያዲስ-አባ ቡና የእወዳይም ጫት
የ Caffeteria ውሎ የሽገር ወጣትን በውስጡ እንጻፈነ
ኢትዮጵያ መሬት ላይ ምንም ነገር ቀረ።
ከወሬ በስተቀር የተረፈን ቢኖር
ምንም . . . ምንም . . . ምንም
ምንም
ነገር ነበር። ምንም . . . ምንም ነገር።
ማውራት ብቻ ጥበብ ሕይወት የሆነባት
እርሷ ኢትዮጵያ ናት።
ኢትዮጵያም ምንም ናት
ማንም የሸመናት
ወርድና ቁመቷን ሳይመዝን ሳይለካት።

29-02-2004

የ _______ ቤት ግጥም

ይድረስ ለሐያሲ . . .
ይሔ የኔ መጽሐፍ
አንተ ዛሬ ደርሰህ . . . አጭር ቁጥብ ምጥን እያልክ የምትከፍለው
የምትሸነሽነው
የምርቆራርጠው . . . መጽሃፍ
የሆነ ጊዜ ላይ
ሠማይ መጠን ሕመም ጽዋ ሙሉ ስንባ ሆኖ የነበረ
የ _______ ቤት ግጥም ነው ብለህ ሥትናገር መስመር ሆኖ ቀረ።

29-02-2004

ዳግም ስለ ትችት

ዘትር ማልጠፋባት አንድ ግሮሰሪ
ዘትር የማይጠፋ አንድ ጎልማሳ አለ
ዕድሜውን የበላ ደብል ጂን እያለ።

እናም የሆነ ቀን
እኔ ቢራ ይዤ እሱም የልማዱን ያንኑ ደብል ጂን
(ያወራኝ ጀመረ)
'እነበብኩት' አለኝ
'እንዴት ነው?' አልኩትኝ
አሪፍ ነው
አሪፍ ነው
አሪፍ ነው። ግን? አለኝ።
ግንን እስኪጨርስ እኔ ዝም አልኩትኝ

ደብል ጂን ደገመ።
'ምን መሰለህ' አለኝ
አሁንም ዝም አልኩኝ
ትንሽ አሰበና
የ'ንትናን መጽሃፍ አይተኸዋል? አለኝ
የማንን ጠየቅኩኝ . . .
ለሰባት ደቂቃ የጠቋሚ ጣቱን አገጩ ላይ አርጎ ሰሙ ጠፋኝ አለኝ
ተወው ተወው ተወው
ስሙን እርሳውና ሐሳቡ ምንድ ነው?
የኔ ጥያቄ ነው? . . .

ሐሳቡ ምንድ ነው?
ዐይኑን ጣርያ ሰቅሎ
እጁን እንጠልጥሎ
ሐሳቡ ምንድን ነው? ትንሽ ቢረሳኝም የሆነ ነገር ነው . . .
ታውቃለህ አይደለ - የሆነ ነገር ነው
ትንሽ ጎምዘዝ ያለው ወሬው ሰላስጠላኝ እንዲህ መለስኩለት
'የሆነ-ነገርን' እኔ አልጻፍኩትም አልኩት
እኔ የምፅፈው
ማንም የትም ምንም ምንም መሆኑን ነው ብዬ ሰናገረው።

ትንሽ ግራ ገባው . . .
ትንሽ ጭንቅ አለው . . .
ሒሳብ ክፍሎ ወጣ

-

ከወራት በኋላ
ስለዚህ ጎልማሳ የሰማሁት ቢኖር
ከወገቡ በላይ ጨርቁን ሜዳጥሎ እንዳበደ ነበር።

30-02-2004

ሐያሲ

አንድ የሆነ ንቀት
ምሑር ለመምሰልም አንድ የእንግሊዝኛ ቃል
እኔን ለመተቸት ለእናንተ ተፈቅዷል
ምክንያቱም ይህ ግጥም እጅጉን አድርጎ ሴቶችን ይጫናል
የሚለው ሰው በዝቷል
-
ደግሞም
ስንተኛው ገጽ ነው?
ምን ነበር የሚለው?
እንዲ እንኳን የሚተች ግጥሜን ያላየው ጆሮ ጠገቡ ነው
ቢሆንም ተፈቅዷል
ለ'ንደዚህ ያለው ግን ተረት ቢጤ አይጠፋም
'ጥንትም ያልተነካ ግልግል አያውቅም'
-
ሌሎች . . .
የሆነ Caffeteria ቡና ቢጤ አዘው
ሁለት ሴት ሦሥት ወንድ ቀዳም ተሰባሰበው
ከሦስቱ አንደኛው
መሐል ያለችውን መጥበስ 'ሚፈልገው
(እንዲህ ይላል)
እኔግን በፊት ላይ እወደው ነበረ
ነበረ
ነበረ
ይኼኛው መጸፍ ግን ግራ ነው ሚገባው
ምን ሊል ፈልጎ ነው
የትም . . . ማንም . . . ምንም . . .እያለ ሚያወራው
(ድንገት አመለጠው)
የሚያሰባት ሴት ልጅ
የትም . . . ማንም . . . ምንም . . . ሚለውን ቃል
ነበር ከልቧ ምትጠላው
እሳት ያልደረሳት
ገና ልጅ ነበረች። ሰሰ . . . ወጣት . . . ቆንጆዬ . . .
ገና ልጅ ነበረች
ይህ ሁሉ ቢሆንም

- ሊጠብሳት ከሰበው ከወንድዬው ግና ፡ . . ‘ምንምን’ በማወቅ
  በ’ልፍ ትበልጣለች

ምክንያቱም ወንድዬው
የትም ማንም ምንም እያለ ሲናገር በጣም ደንግጣለች።
በጣም።

30-02-2004

@Smatch81

@Smatch81

## መውጫ ወዳሻችሁ

ሥትገዙ ግን

አቶልጉን ______________________

ልዩ ምልከት፡

ጸጉሯ የተቆላ ወዛም ብርሃናማ ቡና ይመስል ነበር። ለብቻዋ ጠይም ናት ትንሽ ራሷን ከመታመምዋ በፊት እንደ እርሷ ውብ ብስልና አስተዋይ በቤታችን አልነበረም። ምንም እንኳ እናታችን ከቤት ስትወጣ እኛ ልጆች ብንሆንም እንደ ሕልም ግን ትዝ ትለናለች የአባታችን ያሕል በውል ባናውቃትም የጡቶቿ በረከት ግን በአጥንቶቻችን ውስጥ አለ። አዎ ምንም እንኳ ሊያግት ሲል ብትወልደንም እናታችን ናት። እንደ ሕልም በዝብርቅርቅ የእናታችን ውበት በዓይናችን ፊት አለ።

የተቆላ ብልጭልጭ ወዛም ቡና የሚመስል ጸጉሯ በአረንጓዴ ለምለም ከጫፍ ላይ የተቋጠረ ነው። በርጥብ ቄጤማ የተገመደ ጥቁር። አዘውትራ ፀዐዳ መልበስ ትወዳለች ነጭ እንደ በረዶ። መሃል መቀነቷ በቢጫ አበባ የተሸበበ። የቀሚሷ እግር ከብሯን ያወቀላት ባለሙያ ያነጠፈላት ቀይ ያልሞተ ነገር ግን የተሰዋ ፣ ያልተኮነነ የገደለ ሰማዕት ከብሯን ያስጠበቀበት ደማቅ ቀይ ፣ በሽመና ሳይሆን በሕይወት የተሸመነላት ቀይ የሳባ ጥበብ እግሮቿ ስር ነበር።

ይኸው ድፍን ሰላሳ ስምንት ዓመት ሆናት ትንሽ የነበረች የራስ ምታቷ አዙሪት ሆናባት ከመቼም ተነስታ የትም እርፋ ምንም ሆና መኖር ከጀመረች ድፍን ሰላሳ ስምንት ዓመት . . .

ይኸው ከወጣችበት ርቃ በደረሰችበት ስትበትን ባልተላከችበት ስትደርስ በማትፈልገው ስትውል ሕመሟ አንዳንዴ ሲሻላት አንዳንዴ ሲያገረሽ እናታችን መሆኗን ያወቀ ምዕራብ ናት ሲሉን ስንፈልግ ስናጣት በልጅ ዐይናችን ቢሆንም እንደ ሕልም ቢሆንም ምዕራብ ያየናት ሴት የአባታችንን አፓሬቲቭ መስላ እርሷ ናት አይደለችም? ስንል ደግሞ ሌላ ጊዜ ምስራቅ ታየች ሲሉን ምስራቅ መሃል ምስራቅ ያፈረች የተሸማቀቀች ቀና ማለት ያቃታት ዐይኖቿን ጨፍና እግሮቿን የከፈተች ሲያሳዩን እርሷ ከብረ ሙሉ ልበ ሙሉ ናት ፊቷም ጠይም እንጂ እንዲህ አይደለችም ስንላቸው ታፍሩባታላችሁ? ሲሉን በፍጹም ስንላቸው ልኳን ስንነግራቸው የልጅ ነገር ሲሉን የአባታችንን ስድብ ባዳዎች ሲደግሙት በልጅነታችን አፍረን በአባታችን ተናደን እንደ ሕልም የምናውቃት እናታችን መፈለግ ከጀመርን እርሷም ከወጣችበት ሳትመለስ ይኸው ሰላሳ . . .

ትዝ ይለናል። እንደ ሕልም። እህቴን "ቡና" አፍይልኝ ብላት ከጥበብ ቀሚሷ ልብ ከደረቷ አካባቢ ከጡቶቿ መሃል ብዙ ቡና ስትዘረግፍ የዛለት የተቆላው ቡና ግን ጥቁር ወዛም አልነበርም ቀይ እንደ ደም እንጂ።

ትዝ ይለናል ቡናው ጎመዘዘኝ ስትል የተገነጨችውን እከ ብላ ስትተፋው ከደረቷ መሃል ከጡቷ መካከል በተገኘው ቡና ስታፍር ትዝ ይለናል እንደ ሕልም። እንዳንዴ አባታችን አፕሬቲቭ የሚያበዛው በዚህ ምክንያት ይሆን? እንላለን። እናታችን ከመጥፋቷ አንድ ቀን ቀድሞ በዋዜማው ትዝ ይለናል የተቆላ ወዛም ቡና ከሚመስል ፀጉሯ ላይ አረንጓደውን ለምለም ርጥብ ቄጤማውን በጥሳ ስትጥል . . .

ትዝ ይለናል ፀዐዳዋን ስታወልቅ የሳባውን ጥበብ ስትበጣጥስ

ትዝ ይለናል የወገቧን አደይ ስትበትን ወዳገኘችው . . .

በማግስቱ . . .

ቤቱን ጥላ ስትወጣ ቀትር ነበር ሰዓቱ . . . እናታችንም ያለልማዷ ያለቤታችን ባሕልም ቀይ በቀይ ለብሳ ነበር። ፀጉሯን በቀይ ጠቅልላ ጡቶቿን በቀይ ከልላ ከግንባር እስከ እግሯ ቀይ ነበረች ከባድ ቀይ። ልትጠፋ ከቤት ስትወጣ ደም የለበሰች ትመስል ነበር . . . ይኸው ዛሬ ሰላሳ ስምንት ዓመት የትም መሆን ከጀመረች . . .

አባታችን ለኛ ግድ የለውምና እናታችንን የምታውቁ ወይም ያያችሁ አፋልጉን ፈልጉልን ብዙ ጊዜ ለምን እና በምን እንደሆነ በማናውቀው ምክንያት ቤታችን ሰላም የለውም አባታችን ከኛ ይልቅ ለአፕሬቲቭ ፍቅር ያለው ይመስላል። የሚበላ እያለቀ ነው ስንለው ከሰል ያያይዝልናል ረሃብ ሊጨርሰን ነው ስንለው ቫዝሊን ይሰጠናል . . . አባታችንን አብዝተን ባየነው ቁጥር የእናታችን የዕብደት ምክንያት እርሱ መሆኑ ይገባናል። ባለው በተረፈው ጊዜ እንኳ ከእኛ ይልቅ ለአፕሬቲቮና ለአፕሬቲቭ ጓደኞቹ እጅና ጆሮዎቹ ክፍት ናቸው።

የአባታችን አፕሬቲቭ ጓደኞች . . .

ለምሳሌ . . .

አንድ መራራ ሩሲያዊ ወዳጅ አለው አ . . . እንደ ጂን። ፈረንሳዊ ውሽማ አለችው። እኛም አባታችን በእናታችን ላይ መወሽሙን በአልጋዋ ላይ መባለጉን ብናውቅም ለምን? ብለን ጠይቀነው እናውቅም በቤታችን ከተገዙቱ ነገሮች መካከል ለምን? ብሎ መጠየቅ ነው። ሥለዚህ አንጠይቅም። ቤታችን ከእናታችን መጥፋት በኋላ በፍርሃት የተዳወረ ነው። ደግሞም ፈሪ በመሆናችን ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ በገዛ ቤታችን እንደ አባወራ በመሆኑ የማያፍር የተጨፈገገ ግንባሩ ላይ የአባታችን ዓይኖች ተንከል የተዳፈበት ቀዝቃዛ እንደ በረዶ ከባድ እንደ ውስኪ እንግሊዛዊ ጓደኛ አለው።

አባታችን ለእርሱ ያለው ፍቅር ልዩ ነው። ምናልባት እንግሊዝ ስለተማረ ይሆናል። እኛ ግን እናፍራለን አባታችን ለሦሥቱ ያለውን ፍቅር ያህል ግማሽ ለእኛ ቢኖረው ቤታችን ምንኛ ባማረ። በተዋበ። ወይም አባታችን ለሦሥቱ ያለውን ፍቅር ያክል ሦሥቱ ኩርማኑ ቢኖራቸው ቤታችን የት በደረሰ . . .

ሦሥቱ ግን . . .

ካርታ ሲጫወቱ ሲሳሳቁ ውለው አባታችን ለሽንት ወጣ ሲል የሰማነውን ብንገራቹ

ሁለቱ . . .

እንግሊዛዊውና ፈረንሳዊቷ የአባታችን ውሽማ አባታችን ከአይናቸው ስር ሲርቅ የሆኑቱን መሆን የዶለቱትን መዶለት ብንገራችሁ ምን ዓይነት ቤት ውስጥ ነው የምትኖሩት? ትሉን ነበር . . .

እኛም አብዝተን እንላለን . . .

አባታችንን ያበላሹት እናታችንን ያስደደቷት እኛን ያስራቡን እነዚህ ናቸው? ቀድሞ መራባችንን የፈለጉ ከሆነ ከአገራቸው እኛ ቤት ሲመጡ ለምን ቸኮሌት ይሰጡናል? ለአባታችንስ ብዙ ውስኪ ለምን ያመጡለታል? እንላለን . . . ብለንም እንዲህ እያወራናቸው እንቅልፋችንን እንጠራዋለን . . .

ከአባታችን ወዳጆች ሁሉ አብሶ ከዚህ ጨፍጋጋ እንግሊዛዊ ይልቅ "እያያን" ተኩሶ የሳታት ጣልያናዊው ጎረቤታችን ይሻለናል እንላለን። ታላቅ ወንድሜ ዘወትር አመሻሽ ላይ ይህን ማውራት ይወዳል አባታችን ስለ ኢሕአፓ አውርቶ እንደማይጠግበው ወንድሜም ስለ እያያ እንዲሁ ነው።

የአባታችን የወሬ አዝማች ኢሕአፓ እና ማዕከላዊ ሲሆን የወንድሜ ደግሞ "እያያ" ናት። የኔ ደግሞ አሁን አሁን ፍቅረኛዬ ናት። ቤታችን ትንሽ የተዘበራረቀ ነገር አለው መሰብሰብ ያልቻለ ብትን ዘርፍ የበዛበት ነገር . . .

እያያ እያታችን ስትሆን ከጣልያናዊው ጎረቤታችን ጋር በድንበር ምክንያት ተጣልተው ጣልያናዊው እያታችን ላይ ተኩሶ ይስታታል። እያታችን ግን ደመ መራር ስለነበረች አዘናግታ ጠብቃ በድንጋይ መሃል ግንባሩን ፈንክታው እስከ ዛሬ ድረስ በደካማ ሴት መዋረዱ እንዳይታወቅበት ያለ ኮፍያ አይንቀሳቀስም "ጠባሳው" ግንባሩ መሃል ላይ ያለው ጠባሳ በጣም እጅግ በጣም ትልቅ ነበርና እንደውም እማሆይ ታሪክ ሲነግሩን ጣልያናዊው ጎረቤታችንና እያያን ያስታረቁት እኛ ቤት የሚመጡት የአባታችን አፕሬቲቭ ጓደኞች አባቶች ናቸው ብለውናል። እማሆይ ታሪክ . . .

እኛም ይሄን ሁሉ ታሪክ ብንሰማም ከጣልያናዊው ቆብ ስር ሜዳ መጠን ጠባሳ መኖሩን ብናውቅም ና ቡና ጠጣ ማለታችንን አልተውንም የቤታችን ልማድ ነውና . . .

እንግዲህ አፋልጉን ለማለት ይሄን ሁሉ ዝባዝንኬ ያወራንበት ዋና ምክንያት በአባታችን የአፕሬቲቭ ፍቅር ምክንያት ነው። አባታችን አፕሬቲዞን የሚያዘወትረው ከዚህ ከአማናዊው ድብልትልቅ የቀዳው አመል ሳይሆን አይቀርም ለማለት።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን አባታችንን ከታዘብንበት ምክንያቶች ዋነኛው ለእናታችን መጥፋት ግድየለሽ መሆኑ ነው። የኛም መራብ የሷ መጥፋት ነውና . . .

እኛ ልጆቿ በድንግዝግዝ እንደ ሕልም ትገዝ እያለችን ለምንወዳት ለእናታችን ያለንን ፍቅር ልኩ ልክ እንደሌለው እያወቀ የፍቅራችንን ልክ ቀልድ በሚመስል መራራ እውነት ማጣጣሉና ማናናቁ ነው እንዲህ ሲል በአፕሬቲቭ የታሸ አፋን በሰፊው ከፍቶ እኔም እንደ እናንተ ነበርኩ። እናታችሁ ግን ለሚወዳት አትሆንም። ውሸታም ነው። አባታችን የግል ስህተቱን የሚያከመው ራሱ በሚፈጥረው የቃላት ከምር ነው። እርሱ እናታችንን እኛ የሕልም ያሕል የምናውቃትን ያህል አ.ያ.ው.ቃ.ት.ም . . .

እናንተ የምታውቋት አፋልጉን ምክንያቱም ጠፍታብናለች። . . .

እናንተ የምታውቋት አፋልጉን ምክንያቱም ልንጠፋ ነውና። በቤታችን ሰንጣቃ መስኮት ስር የተሰፋ ኮከብ ይታየናል። አፋልጉን!

አይቀርም። . . .

እናታችን ሕልም ከሚመስል እውቀታችንና ፍቅራችን ወደ አካልና እውነታዊነት ትመልሰናለች። ይህች በልባችን የቀረችው የመጨረሻዋ ተስፋችን ናት የጠፋው እንደሚገኝ የራቀው እንደሚቀርብ የምታሳይ ብርሃን ሆናናለች።

ስለዚህ በዚህ ተስፋ ስር መሆናችንን የምታውቁ እናታችን የደረሰችበትን የምታውቁ የሰማችሁና ያያችሁ እዚህ-ነች በሉን።

ምልክቷ በድጋሚ . . .

የተቆላ ወዛም ቡና መስል ጸጉሯ ላይ ለምለም አረንጓዴ ቁጤማ የታሰረ አለ። ፀዐዳ ተመራጭ ልብሷ ነው። ወገቧ በደማቅ ቢጫ በአደይ የተሸበበ። ቢጫው መሃል ማህጸኗ አካባቢ በኮከብ ፈርጥ የደመቀ። እግሮቿ ዙሪያ ያልሞተ ነገር ግን የተሰዋ የጠለፈላት ቀይ የሳባ ጥበብ ያልተኮነነ የገደለ ሰማዕት ከብሯን ያስጠበቀበት ደማቅ ቀይ በከር ሳይሆን በሕይወት የተሸመነላት ቀይ የሳባ ጥበብ እግሮቿ ስር አለ። . . .

ልዩ ምልክት

እናታችን ከብረ ሙሉልበ ሙሉ ናት። እንኳንስ በአዘቦት ለበዓል በጭፈራና በዳንስ ጊዜ እንኳ ልብሷ ጥበብ ነው ውዝዋዜዋ ከንብንዘ ውስጥ ነው። ይህችን ጠይም ይህችን ሴት ይህችን እናት አፋልጉን በዚህም ደውሉልን።

66 . . . የቤት ስልክ ሲሆን አገልግሎት ስለማይሰጥ በተንቀሳቃሽ 2005 ብላችሁ ደውሉ

ፈላጊዎች

ትውልድ ይቀጥላል . . . አሁን

እስከዚያው እናታችን በብራናዋ ላይ ካወረሰችን (ትታው ስትሄድ ካገኘነው) ውርስ መካከል በደምዋ የተጋባብንን ቅኔ እነሆ። ያለንን እንደ ወርታ ስለምታቋልትን እንደ መያገር ይሆንልን ዘንድ እነሆ ቤታችንን በሰፊው አሳየናችሁ።

ልጆቿ

ለአባቶች . . .

<u>ገልባጭ</u>

ለየትም

ለማንም

ለመቼም

ለምንም

ይቅርታ . . .

የሆነ የስልክ ጥሪ ይሰማኛል።

ሃሎ? . . .

ሃሎ! . . .

ሃሎ። . . .

ኤፍሬም ስዩም ተሰማ ነኝ

ሠላም

## የአርቲስቱ ስራዎች

* ሶልያና የግ ጥም አልበም - ግ  ጥምና ሙዚቃን በ  ማዋሃድ የተ ሠራ 1998 ዓ.ም.

* ሙዚ - ቃል  (የብርሃን ከንፎች ) ሙዚቃና ግ ጥምን በማዋሃድ የተ  ሠራ (Experimental) አልበም 2004 ዓ.ም.

አሳታሚ

YISAKAL ENTERTAINMENT

VISUALIZE CREATE REVIVE INSPIRE ENTERTAIN

ብር 37.50 USD 20

ዜድ. ኤ ማተሚያ ቤት